# ገዲር ላይ ምን ተከሰተ?

## የነብዩ ሙሐመድ  የመጨረሻው ንግግርና ኑዛዜ


በ መሐመድ ባቂር አንሷሪ

ትርጉም፡

ጣሂር መሐመድ ዓሊ አል-ጎዳነምቢ



2003/2011

# ገዲር ላይ ምን ተከሰተ?

**ታላቁ ጉባዔ**

**ታሪካዊ ንግግር**

**የቃለ መሐላ ሥነ ሥርዓት**

**በአሥራ ስምንተኛው ዙልሂጃህ፣ 10ኛው ዓመተ-ህጅራ**

**የገዲር ኹም ክስተትን በአጭሩ**

**ለመግለጽ የተደረገ ሙከራ**

**የተባረከው  የገዲር ዕለት ሙሉ የኹጥባ ጽሁፍ**


በ መሐመድ ባቂር አንሳሪ

ትርጉም፡

ጣሂር መሐመድ ዓሊ አል-ጎዳነምቢ

## *እጅግ ርህሩህና አዛኝ በሆነው በአላህ ስም*

*መታሰቢያነቱ፡-*

- *ለ የታላቁ ነብይ ቀጥተኛው መንገድ ፈላጊዎች፣*
- *የገዲር ክስተትን ዘለዓለማዊ እውነታ ላልሰሙ፣*
- የገዲርን ክስተት ላልሰሙት ለማሰማት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ያቀረቡትን ጥሪ በመቀበል፣ በዕለቱ ላልነበሩ ሰዎችና ለመላው ትውልድ ለማብሰር እንዲሁም ይህን ታሪካዊ ክስተትና የእምነታችን አስኳል ወደ ተግባር ለመለወጥና እውን ለማድረግ፣ ይህንን ሙከራዬን በስጦታ አቀርባለሁ፡፡

**ማውጫ** **ገጽ**


መቅድም-------------------------------------------------------------------7

ገዲር እምነት ነው-------------------------------------------------------7

ይህ መጽሐፍ-------------------------------------------------------------8

**1. የገዲር ኹም ክስተቶች ጥቅል ዳሰሳ**--------------------------------------10

የሐጅ ሥርዓትና ቀጣዩን የመሪነት ጉዳይ አስመልክቶ

የመጣ አዋጅ/ትዕዛዝ------------------------------------------------------ 10

የሐጁ ሥርዓት------------------------------------------------------------ 11

የማዕረግ ስም - አሚሩል ሙእሚኒን--------------------------------------- 12

ለገዲር ኹም ጉባዔ አጠቃላይ ጥሪ-----------------------------------------12

የሙስሊሞች በገዲር ኹም መሰብሰብ--------------------------------------14

ህዝባዊ ንግግሩ ከመጀመሩ በፊት የነበሩ እንቅስቃሴዎች--------------------15

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ህዝባዊ ንግግሩን ያደረጉበት አኳኋን---------------------- 15

መድረኩ ላይ የተወሰዱ ሁለት ተግባራዊ እርምጃዎች---------------------- 16

**አንደኛ፡**- ዓሊን ከፍ ማድረግና ለይቶ ማውጣት--------------------------- 16

**ሁለተኛ፡**- በእጅ በይዓ ከማድረግ በተጨማሪ በልብና

በምላስ ቃል መሐላ/ቃል ኪዳን (በይዓ) መፈጸም----------------------------17

በገዲር ኹጥባ ነብዩ ያስተላለፉት መልዕክት በጥቅሉ ሲታይ-----------------19

ከኹጥባው ቀጥሎ የነበሩ ሥነ-ሥርዓቶች------------------------------------25

የወንዶች ድምጽ አሰጣጥ (በይዓ አደራረግ) ሥርዓት------------------------25

የሴቶች ድምጽ አሰጣጥ (በይዓ አደራረግ) ሥርዓት--------------------------28

የነብዩ ጥምጣም------------------------------------------------------------28

የገዲር ግጥም---------------------------------------------------------------29

ጂብሪል (ገብርኤል) በገዲር---------------------------------------------------31

የገዲር ተዓምር------------------------------------------------------------------32
የኢስላም ኃይማኖት ገዲር ላይ ፍጹምና ምሉዕ ሆነ----------------------------33
የገዲር ኹጥባ ሥነ -ሥርዓት መጠናቀቅ------------------------------------------35
**2. ኢብሊሶችና ሙና ፊቆች በገዲር-----------------------------------------37**
ኢብሊሶች በገዲር------------------------------------------------------------------37
ሙናፊቆች በገዲር-------------------------------------------------------------------38
የመጀመሪያው ሴራ---------------------------------------------------------------39
ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ለመግደል የተሸረበ ሴራ----------------------------------------39
ሁለተኛው ሴራ--------------------------------------------------------------------41
**3. የገዲር ኹጥባ ዓላማዎች በአጭሩ-------------------------------------------43**
የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ንግግር አስኳል-----------------------------------------------43
በኹጥባው ላይ የተነሱ ርዕሶች አኃዛዊ ትንተና-------------------------------44
ሀ. የኹጥባው አበይት ርዕሶች---------------------------------------------------44
ለ. በኹጥባው ወስጥ የተጠቀሱ የተባረኩ ስሞች------------------------------45
ሐ. በኹጥባው ውስጥ የተጠቀሱ የቁርአን አንቀጾች----------------------------46
**4. በገዲር ኹጥባ ዙሪያ ያሉ ጥናቶችና ትንታኔዎች---------------------------47**
የገዲር ኹጥባ ዋቢ መጽሐፍት (Bibliography) -------------------------47
የኹጥባው ዋቢ መጽሐፍትና የዘገባ ሂደት---------------------------------------50
የኢማም ሙሐመድ አል-ባቂር ሪዋያ በሁለት ሰነዶች---------------------------51
የዘይድ ቢን አርቀም ሪዋያ በአንድ ሰነድ-------------------------------------52
የሁዘይፋ ቢን አል-የማን ሪዋያህ በአንድ ሰነድ--------------------------------52
የኹጥባው ጽሁፍ ግምገማ-------------------------------------------------------53

**5. የገዲር ኹጥባ**-----------------------------------------------------------**54**

**ክፍል አንድ** አላህን ማመስገንና ማወደስ-------------------------------------54

**ክፍል ሁለት** ከአላህ የመጣን እጅግ ጥብቅ

ትዕዛዝ የማስተላለፍ ዝግጅት-----------------------------------------------58

**ክፍል ሦስት** የዓሊ ቢን አቢ ጣሊብንና ቀጥሎ

የሚመጡትን የአስራ ሁለት ኢማሞች መሪነትና

ኢማምነትን በግልጽ ማወጅ----------------------------------------------------61

**ክፍል አራት** ነቢዩ(ሰ.ዐ.ወ) የአሊን እጅ ከፍ አድርገው ያዙ--------------------67

**ክፍል አምስት** የህዝቡን ትኩረት ወደ ኢማምነት

(ኢማማህ) ጉዳዮች መሳብ----------------------------------------------------69

**ክፍል ስድስት** የሙናፍቆችን ዓላማና ሐሳብ መጠቆም--------------------------71

**ክፍል ሰባት** የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) አህለልቤይት ( ቤተሰቦች)

ወዳጆችና ጠላቶች----------------------------------------------------------76

**ክፍል ስምንት** ኢማም አል-መህዲ---------------------------------------------79

**ክፍል ዘጠኝ** ሰዎች ቃል-ኪዳን እንዲገቡና ምስክርነታቸውን

እንዲሰጡ (በይዓ እንዲያደርጉ) ማነሳሳት----------------------------------------81

**ክፍል አስር** የኃይማኖት ህግጋት መጠናቀቅና የኢማሞቹ ሚና-----------------82

**ክፍል አስራ አንድ** ቃል- ኪዳኑን በቃል ማሰማትና በይዓ

(ቃለ-መሐላውን) መቀበል----------------------------------------------------86

ኢድ አል-ገዲር (የገዲር በዓል) ---------------------------------------------90

የገዲር በዓል በታሪክ ውስጥ-------------------------------------------------90

የገዲር በዓል እጅግ አስፈላጊነት------------------------------------------------91

በበዓሉ ዕለት የሚደረጉ ነገሮች-----------------------------------------------93

የመጨረሻ ቃል-------------------------------------------------------------------------94
የነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የመጨረሻው
ህዝባዊ ንግግር (ኹጥባ) ሙሉ የዐረቢኛ ጽሁፍ-----------------------------------95
ዋቢ መጻሕፍት--------------------------------------------------------------------123

# እጅግ አዛኝና ርህሩህ በሆነው በአላህ ስም

## መቅድም

### *ገዲር እምነት ነው*

ገዲር የእምነታችን ዐርማ ነው፡፡ ገዲር የኢስላም ህልውናና የነብዩ ሙሐመድ ነብይነት ፍሬ ነው፡፡ ገዲር ታሪካዊ ክስተቱ ብቻ እየተወሳ የሚኖር ሳይሆን እያንዳንዱ ሙስሊም መከተል የሚገባው የህይወት መስመር ነው፡፡ የገዲር ህዝባዊ ንግግር (ኹጥባ) የአሚረል ሙዕማኒን ዓሊ መሪነት የታወጅበት ህያው መዝገብ ነው፡፡

ከዕለተ-ገዲር በፊት፣ በዕለተ ገዲርና ከዚያ በኋላ የተከሰቱትን ድርጊቶች በመጥቀስ አጠቃላይ የሆነ የገዲር ክስተት ገጽታ ይቀርባል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በኢስላም አጠቃላይ የታሪክ ትንተኔና ግንዛቤ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ በርካታ ጉዳዮችና እውነታዎች፣ በተለይ ደግሞ ከነብዩ ህልፈት በኋላ የተከሰቱ ድርጊቶችን በግልጽ ያወጣል፡፡

የገዲርን ህዝባዊ ንግግር መረዳትና ጠብቆ ማቆየት አስፈላጊነትና ያለበትን ኃላፊነት ለመረዳት ህዝቡ የተሟላ ንግግሩንና እያንዳንዱን ክስተት መረዳት ይገባዋል፡፡ በተጨማሪም ህዝቡ ይህን ታሪካዊ ክስተት እንደ ከፍተኛ የኢስላም ህግ በማየትና በኃይማኖታችን ውስጥ እጅግ ወሳኝ የሆነ የታሪክ ምዕራፍ እንደሆነ በመረዳት የዚህ ህዝባዊ ንግግር ጽሁፍ ኮፒ መያዝና ጠብቀው ማቆየት አለባቸው፡፡

ከዚህ አንፃር የገዲር ህዝባዊ ንግግር (ኹጥባ) በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መለኮታዊ ተልዕኮ ዓመታት ውስጥ ከፍተኛውን ቦታ የሚይዝ በነብዩ የተደረገ ታላቅ ኢስለማዊ ንግግር ነው፡፡ ይህ ውድ መዝገብ ለኢስላም ዘለዓለማዊ ንግግር ነው፡፡ ይህ ውድ መዝገብ ለኢስላም ዘለዓለማዊ ሉዓላዊነት የሚቆም እስከ ሆነ ድረስ በጽሁፍ መልክ የቀረቡትን ኮፒዎች መመርመር፣ ማጥናት፣ ኮፒዎችን ማነጻጸርና በተቻለ መጠን ጥሩ በሆነ መልኩ ማስታዋወቅ ይገባል፡፡

## ***ይህ መጽሐፍ***

ይህ መጽሐፍ የገዲር ክስተትን አብይ ጉዳይና ሌሎችንም ተጨማሪ ዝርዝር ጉዳዮች አካቶ ያቀርባል፡፡ ቀጥሎ አጠቃላይ የገዲርን ህዝባዊ ንግግር ጽሁፍ ያቀርባል፡፡

ይህ ሥራ አጠቃላይ ንግግሩንና እያንዳንዱን ክስተት በዝርዝር ካስቀመጥኩት ***አሥራር ገዲር*** ከተሰኘው ሥራዬ ተጨምቆና ተቃሎ የቀረበ ነው፡፡ እዚህ ለተጠቀሱት ሐዲሶችና አባባሎች ዋቢ መጽሐፍትንና ምንጮችን ለማጥናት የፈለገ ሰው እላይ የተጠቀሰውን መጽሐፍ ማማከርና መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም ዋቢ መጽሐፍትና ምንጮች በመጽሐፍ መጨረሻ ላይ ተዘርዝረዋል፡፡

ይህ መጽሐፍ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መልዕክቱ ለሁሉም ትውልድ ይደርስ ዘንድ ያደረጉትን ጥሪና የሰጡትን ኃላፊነት በመቀበልና ምላሽ በመስጠት፣ እስከ አሁን ያልሰማ ወገንና ቀጣዩ ትውልድም ይሰማ ዘንድ የገዲርን ታሪካዊ ክስተት አስመልክቶ በአጭሩ ያቀረበ ነው፡፡

ይህንን በኢስላም ታሪክ ውስጥ ታላቅ የሆነ ቀንና በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የተደረገውን እጅግ ወሳኝ ህዝባዊ ንግግር ለመዘከርና ተገቢውን ክብርና ትኩረት ለመስጠት በአመት አንዴ እንዲከበርና እንዲጠና ለመላው ሙስሊም የተበረከተ ዕድል ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ይህንን ጉዳይ በተመለከተ፣ ይህንን ክስተት ከማያውቁትና በአዕምሮም ሆነ በአካል ከዚህ ክስተት ርቀው ከሚገኙ ሰዎች በፊት ሙስሊሞች ዘገባዎችን መጠበቅና ማቆየት አለባቸው፡፡ የኢስላምን ዘለዓለማዊ ተልዕኮና መልዕክት የማስተላለፍና የማዳረስ ተግባር የሆነውን የኢማሙን ኃላፊነት በከፊል ማሟላት አለባቸው፡፡

ይህ መጽሐፍ ጠቃሚና ተቀባይነት ያለው ይሆን ዘንድ ከሁሉ በላይ የሆነውን ፈጣሪ እማጸናለሁ፡፡ በኃይማኖታዊ ዕውቀት ውስጥና በወዲያኛው ዓለም ሰዎች የሚጠየቁበት ኢስላማዊ መመሪያዎችን አስመልክቶ ጠቃሚ ሚና የሚጫወት ሥራ እንዲሆን ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አህለል ቤይት (ቤተሰቦች) (ዐ.ሰ) መሪነት ካመኑትና ከተከተሉት ወገኖች ጋር ለሚደብለን አላህ ምስጋናና ውዳሴ የሱ ነው፡፡

መሐመድ ባቂር አንሳሪ ዘንጃኒ ኹይኒ

ቁም፣ ዕለተ ገዲር፣ 1420

ማርች 25,2000

የአማርኛ ትርጉም፣

ጣሂር መሓመድ ዓሊ አል-ጎዳነምቢ

መጋቢት 2003/ አፕሪል 2011

# 1

# *የገዲር ኹም ክስተቶች ጥቅል ዳሰሳ*

በመቀጠል ከዕለተ ገዲር በፊትና በኃላ የተከሰቱ ድርጊቶችንና ህዝባዊ ንግግሩ የተዳረገበትን አኳኋን በማስመልከት ጠቅለል ባለ ሁኔታ ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡ ከአላህ የተሰጠውን ትዕዛዝ በመቀበል ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ካደረጉት ተግባራት አጠቃላይ አዋጅ እንጀምር፡፡

## *የሐጅ ሥርዓትና ቀጣዩን የመሪነት ጉዳይ አስመልክቶ የመጣ አዋጅ/ትዕዛዝ*

ታላቁ ነብይ (ሰ.ዐ.ወ) ወደ መዲና ከተሰደዱ ከአሥር ዓመታት በኋላ መለኮታዊ ትዕዛዝ ተገለጠላቸው፡፡ ይህ የኢስላም የመጨረሻውን ጥያቄ የሚመለከት ነበር፡- **የሐጅ ሥርዓትና የአሥራ ሁለቱ ኢማሞች ኢማምነት**፡፡

የሐጅን ሥርዓት አስመልክቶ አጠቃላይ አዋጅ በመነገሩ 120 ሺህ ሙስሊሞች ከተለያዩ ቦታዎች ወደ መካ ተመሙ፡፡ በመስጂድ አል-ሸጀራህ የሀጅ አድራጊዎች ዩኒፎርም ከለበሱ በኋላ፣ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከሰሃቦቻቸው ጋር በመሆን ወደ መካ አቀኑ፡፡ በአምስተኛው ዙል-ሂጃህ እዛ ደረሱ፡፡

በወቅቱ በየመንና ነጅራን የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ተወካይ የነበረው አሚሩል ሙዕሚኒን ዓሊ የሐጅ ዩኒፎርም ለብሶ መካ ሲገባ አሥራ ሁለት ሺህ የመናዊያንን አስከትሎ ነበር፡፡

## የሐጅ ሥርዓት

የሐጅ ሥርዓቱ ቀን ሲደርስ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ወደ አረፋት፣ አል-መሽዕሪል ሐራም እና ሚና በማቅናት የሐጅን ሥርዓት በቅደም ተከተል ፈጸሙ፣ በሥርዓቱ ውስጥ የሚፈቀዱና የማይፈቀዱ ተግባራትን ለይተው ህዝቡን አስተማሩ፡፡
ዓሊ የሙዕሚኖች ኃይማኖታዊና ፖለቲካዊ መሪ ሆኖ መመረጥ እንዳለበትና የነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ኃላፊነት ተረክቦ በተተኪነት መሰየም እንደሚገባው የሚደነግግ ትዕዛዝ በአረፋት ተራራ ላይ ለነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ወረደ፡፡ ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) ትዕዛዙን ተቀብለው ወዲያው ተገበሩት፡፡

ሚና ላይ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከፍ ባለ ድምጽ ሁለት ጊዜ ለፈፉ፡፡ የጥሪው ዓላማ ዓሊን ተተኪያቸው አድርገው መሰየም ነበር፡፡ በመጀመሪያው ንግግራቸው እሳቸው (ነብዩ) በሌሉበት ሁኔታዎችና አጋጣሚዎች በመሉ ዓሊ ተወክሎ ሲሰራ መክረሙን አስታወሱ፡፡ በተጨማሪም ሁለቱን ሚዛን የሚደፉ/ሰቀለይን (ውድና ከባድ የሆኑ) ነገሮችን በማውሳት ሙስሊሞችን አስታወሱ፡- “ሁለት የከበሩና የከበዱ ነገሮችን በመካከላችሁ ትቼላችኋለሁ፣ እነዚህም የአላህ መጽሐፍ (ቁርአን)ና የኔ አህለል-ቤይት (ቤተዘሮቼ) ናቸው፡፡”

አል-ኼይፍ መስጂድ ውስጥ ያደረጉት ሁለተኛው ንግግራቸው ደግሞ የሙስሊሞቹን አዕምሮና ትኩረት ወደ ዓሊ ኢማምነት (መሪነት) መሳብ ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ ከዚያም በላይ ንግግራቸውን በጥሞና ማዳመጥ እንዳለባቸውና መልዕክቱን ላልሰሙት በሙሉ ማድረስ እንዳለባቸው በአጽንኦት አስጠነቀቁ፡፡

## *የማዕረግ ስም- አሚሩል ሙእሚኒን*

ሙስሊሞች ወደ መካ ከተመለሱ በኋላ መላኢካው ጅብሪል አላህ ለዓሊ ኢብን አቢ ጣሊብ ***አሚሩል ሙእሚኒን*** የሚል የማዕረግ ስም እንደሰጠው አበሰረ፡፡ በዚህ መሠረት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰሃቦቹ ተሰብስበው ለዓሊ ሠላምታ እንዲያቀርቡና "አሚሩል ሙዕሚኒን" በሚለው የክብር ስም እንዲጠሩት ትዕዛዝ አስተላለፉ፡፡

እነሱም በሰልፍ ሆነው ተራ በተራ፡- "ሰላም ለአንተ ይሁን አሚሩል ሙዕሚኒን ሆይ" በማለት ትዕዛዙን ፈጸሙ፡፡

## *ለገዲር ኹም ጉባዔ አጠቃላይ ጥሪ*

የሐጅ ሥነ-ሥርዓቱ ከተጠናቀቀ በኋላ አላህ ቀጥሎ ያለውን የቁርአን አያህ አወረደ፡-

**“ነብዩ ሆይ! ከጌታህ የተወረደልህን (መልዕክት) አድርስ! ይህንን ካላደረግክ መልዕክቱን (በሙሉ) አላደረስክም፡፡ አላህ ከሰዎች ይከላከልሃል (ይጠብቅሃል)፡፡ በእርግጥም አላህ እነዛን ያላመኑትን አይመራም፡፡”**

ስለዚህ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አዋጅ የመናገርና ጥሪ የማድረግ ኃላፊነት የተሰጠውን ቢላልን ጠርተው በሚቀጥለው ቀን ህዝቡ በሙሉ በገዲር ኹም ላይ መገኘት እንዳለባቸው እንዲያውጅ አዘዙት፡፡

“ገዲር ኹም” የሚባለው ቦታ ከጁህፈህ ቀጥሎ ያለ ቦታ ነው፡፡ ወደ መዲና፣ ግብጽ፣ ኢራቅ፣ ሶሪያና ነጅድ የሚሄዱ መንገዶች የሚገናኙበት ቦታ ነው፡፡ መለኮታዊ ትዕዛዙን በመቀበል ይህ ቦታ የተመረጠው ውኃና የተወሰኑ ዛፎች ያሉበት አካባቢ ስለሆነ ነው፡፡ በጉዞ ወቅት መንገደኞች እንደማረፊያነት የሚጠቀሙት የተለመደ ቦታ ነበር፡፡

እነዚህን ቀናት ለመዘከር የአምልኮ ሥርዓቶች የሚከናወኑበትና በየጊዜው የሚጐበኝ ለብዙ ምዕተ ዓመታት የኖረ አል-ገዲር የሚሰኝ መስጂድ ነበረ፡፡

ነብዩ ያለ ወትሮው ወደዛ ቦታ በማቅናታቸው ህዝቡ ተግርሞ በቅርብ ርቀት ለመከተል ራሳቸውን አዘጋጁ፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከሐጅ ሥነ-ሥርዓት በኋላ መካ ውስጥ የመቆየት ልምድ ነበራቸው፡፡ ምክንያቱም በመካ ቆይታቸው ወቅት እንግዶችን (ጐብኚዎችን) ተቀብለው የተለያዩ አስተያየቶችን እየሰሙና እያስተናገዱ፣ የህዝቡን ጥያቄዎች በመመለስና ችግሮቻቸውን በመቅረፍ ተግባር ተጠምደው ለተወሰኑ ቀናት በከተማዋ ይቆዩ ነበር፡፡ በመጨረሻው (በመሰናበቻው) የሐጅ ሥርዓት ወቅት ግን ሳይቆዩ ወደ ገዲር ኹም አቀኑ፡፡

## *የሙስሊሞች በገዲር ኹም መሰብሰብ*

በዛን ዕለት ጧት 120 ሺህ ሙስሊሞች ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር በመሆን ወደ ገዲር ኹም ተመሙ፡፡ የደረሳቸው ዜና እጅግ ጠቃሚና አሳሳቢ መሆኑን ስለሰሙ አሥራ ሁለት ሺህ የመናውያን (የየመን ሰዎች) መንገዳቸውን ቀይረው ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ተከትለው ወደ ገዲር ኹም አቀኑ::

በቦታው እንደደረሱ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ህዝቡ ጉዞአቸውን ገተው ይቆሙ ዘንድ እዋጅ እንዲነገር ትዕዛዝ ሰጡ፡፡ ከቦታው ያለፉ ሰዎች ወደ ኋላ እንዲመለሱ፣ ወደ ኋላ የቀሩ ሰዎች እንዲጠበቁና ሁሉም ሰው አላህ በመረጠው በዛ ቦታ እንዲሰባሰብ ጭምር አሳሰቡ፡፡ በተጨማሪም በትላልቅ ዛፎች ሥር በመከለል ከእይታ ውጭ የሆኑ ሰዎች ወደ ገላጣ ቦተ እንዲቀርቡና ለቀጣይ ሶስት ቀናት ለሚደረገው ሥነ -ሥርዓት ቦታው መጽዳትና መዘጋጀት እንዳለበት ትዕዛዝ አስተላለፉ፡፡

በዚህ አኳኋን ወደ ገዲር የተመመው ቅፍለት በሙሉ እያንዳንዳቸው ቦታ ቦታቸውን ያዙ፡፡ ይህ ሁሉም ሰው እስኪረጋጋና እስኪሰክን ድረስ ቀጠለ፡፡ ወቅቱ ኃይለኛ የፀሐይ ሀሩር የነበረበት እጅግ ሞቃት ጊዜ ስለነበረ ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ጨምሮ እያንዳንዱ ሰው ራሱንና አግሮቹን በልብስ ይሸፍኑ ነበር፡፡ ሌሎቹ ደግሞ እግሮቻቸውን በጨርቅ ጠቅልለው ነበር፡፡

## *ህዝባዊ ንግግሩ ከመጀመሩ በፊት የነበሩ እንቅስቃሴዎች*

ሰልማን፣ አቡ ዘር፣ አል-ሚቅዳድና አማር የነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ትዕዛዝ በመቀበል በትላልቅ ዛፎች ሥር ያለውን ቦታ ማጽዳትና መጥረግ ያዙ፡፡ በዛፎቹ ሥር የበቀሉትን እሾሆች ነቀሉ፣ ድንጋዮችን አነሳሱ፣ ቦታውን ጠርገው ውኃ አርከፈከፉ፡፡ ከዚያም ለጥላ ይሆን ዘንድ ጨርቅ ወስደው አንዱን ጫፍ በአንዱ ዛፍ ላይ ሌላኛውን ጫፍ ደግሞ በሌላኛው ዛፍ ላይ አሰሩ፡፡ በዚህ ሁኔታ ለቀጣይ ሶስት ቀናት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የአዋጅ ሥነ-ሥርዓቱን የሚየደርጉበት አመቺ ቦታ ተዘጋጀላቸው፡፡

በዛፎቹ ጥላ ሥረ ድንጋዮችን በመሰብሰብና በመከመር፣ የግመል ኮርቻዎችንም በመጠቀም ከፍ ያለ መድረክ ተሠራ፡፡ የመድረኩ ከፍታ የነበዩን (ሰ.ዐ.ወ) ቁመት ያህል ነበር፡፡ መድረኩንም በጨርቅ ሸፈኑት፡፡ መድረኩ የተሠራው ከተሰበሰበው ህዝብ መሐል ላይ ሆኖ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለሁሉም እንዲታዩና ድምጻቸውም በተቻለ መጠን ለሁሉም ሰው እንዲሰማ ታስቦ ነበር፡፡ ራቅ ብለው ለተቀመጡ ሰዎች የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ቃላት እንዲሰሙ በማሰብ አንድ ሰው የነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ቃላት በመድገም እንዲያሰማ ተደርጐ ነበር፡፡

## *ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ህዝባዊ ንግግሩን ያደረጉበት አኳኋን*

ህዝቡ ከዛ በላይ መጠበቅ ስለማይችል የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሙአዝን ከህዝቡ ውስጥ ወጣ በማለት ለጀመዓ ሰላት ጥሪ አደረገ፡፡ መድረኩ ፊት ተሰልፈው በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መሪነት ዙህር (የቀትር ሰላት) ተሰገደ፡፡

ከዚያም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በመድረኩ ላይ ቦታቸውን ሲይዙ ህዝቡ ተመለከተ፡፡ ኹጥባው ከመጀመሩ በፊት ዓሊ በቀኛቸው እንዲሆን አደረጉ፡ ዓሊ በነብዩ ጐን በቀኛቸው በኩል ቆመ ፡፡ ነገር ግን ከነብዩ ትንሽ ዝቅ ብሎ ነበር የሚታየው፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የህዝቡን መሰብሰብ ይጠብቁ ይመስል አይኖቻቸውን መጀመሪያ ወደ ቀኝ፣ ከዚያም ወደ ግራ አማተሩ፡፡ ሰዎች ለማዳመጥ ልክ እንደተዘጋጁ ኩጥባውን (ህዝባዊ ንግግሩን) ጀመሩ፡፡ ለሰው ልጅ ያደረጉት የመጨረሻው ኹጥባ (ንግግር) ነበር፡፡ ስለ ቦታውና መድረኩ እንዲሁም ስለ ኩጥባው አጠቃላይ አካሔድ ይህን ያህል ካልን በመቀጠል ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ያደረጉት ወደ ገዲር ኹጥባ እንሄዳለን፡፡

## *መድረኩ ላይ የተወሰዱ ሁለት ተግባራዊ እርምጃዎች*

ንግግር የሚደረገው ቃላትን በመጠቀም ብቻ መሆኑ የተለመደ ቢሆንም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የታዳሚውን ትኩረት በግልጽ የሳቡ ሁለት ተግባራዊ እርምጃዎችን ወሰዱ፡፡ ኩጥባውን በአጭሩ ከማቅረባችን በፊት እነዚህ ሁለቱን እርምጃዎች ማቅረብ ጠቃሚ ይሆናል፡፡

## *አንደኛ፡- ዓሊን ከፍ ማድረግና ለይቶ ማውጣት*

ወደፊት ሊከሰቱ የሚችሉትን አንዳንድ ጥርጣሬዎች ለማጥፋት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዓሊን ለይተው በተግባር አሳዩ፡፡ ይህ የሆነው የዓሊን እዛ ቦታ የመቆም ሚስጢርና አሳቸውን ተክቶ ኃይማኖታዊና ፖለቲካዊ መሪነቱን የሚረከብ መሆኑን ልክ ከተናገሩ በኋላ ነበር፡፡

ከዚያም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)፡- "ይህ እጁን ይዤ ወደ ላይ ከፍ ካደረኩት ሰው ሌላ፣ ይህ እጁን በሁለት እጆቼ ይዤ ከፍ አድርጌ ከማሳያችሁ ሰው ሌላ የቁርአንን ሚስጢርና ዝርዝር ጉዳዮችን እንዲሁም የሚያስጠነቅቁና አስፈላጊ ጉዳዮችን በጥልቀትና በዝርዝር ሊነግራችሁና ሊያስተምራችሁ የሚችል ማንም ሰው የለም፡፡" በማለት በግልጽና በተግባር በማሳየት ተናገሩ፡፡

ዓሊን ይዘው ወደ ላይ አነሱ፡፡ ዓሊም እጆቹን ወደ ሰማይ ከፍ አድርጎ ዘረጋ፡፡ በዚህ ሁኔታ እያሉ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የዓሊ እግር ጉልበታቸው ድረስ እስኪደርስ ከፍ አድርገው ያዙት፡፡

በዚህ ጊዜ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ አሉ፡-

"እኔ ወሊይ (መሪ/አዛዥ) የሆንኩት ማንኛውንም ሰው ሁሉ፣ ይህ ዓሊም ወሊዩ (መሪው/አዛዡ) መሆን አለበት፡፡ አላህ ሆይ! እሱን የሚደግፍን ሁሉ ደግፈው፣ እሱን የሚቃረንን ተቃረነው፣ ለረዳቶቹ ድልን አጐናጽፍ፣ እሱን በሚየስቆጡት ላይ ቁጣህ ይውረድባቸው፡፡"

## ***ሁለተኛ፡- በእጅ በይዓ ከማድረግ በተጨማሪ በልብና በምላስ ቃል መሐላ/ቃል ኪዳን (በይዓ) መፈጸም***

የህዝቡ ቁጥር እጅግ በርካታ ከመሆኑ የተነሳ ቀደም ሲል በተለመደው መልኩ የተመራጩን እጅ በመጨበጥ ቃል ኪዳን መግባት (በይዓ ማድረግ) የማይቻል ነበር፡፡ አንዳንድ ሰዎች ደግሞ ያንንም ካደረጉ በኋላ ወደ ኋላ ይመለሱ ነበር፡፡ ስለዚህ በንግግራቸው ማጠቃለያ አካባቢ ነብዩ ሲናገሩ፡- "ሰዎች ሆይ!

ከሁላችሁም ጋር በአንዴ ለመጨባበጥ እጅግ ብዙ ስለሆናችሁ አይመችም፡፡ ለዓሊ የሰጠሁትን ሹመትና ከሱ ቀጥሎ ለሚመጡት ኢማሞች የተሰጠውን ቦታ በአጠቃላይ መስማታችሁንና መቀበላችሁን፣ የኔ አህለል ቤይት (ቤተሰቦች) ከዓሊ አብራክ የሚገኙ መሆናቸውን እንደነገርኳችሁና እንደ ተቀበላችሁ የሚያረጋግጥ ቃላችሁን በአፋችሁ በማሰማት ቃል ኪዳን መግባታችሁን (በይዓ ማድረጋችሁን) ቃላችሁን እንዲቀበል ከሁሉ በላይ የላቀው ጌታ አዞኛል፡፡ ስለዚህ ሁላችሁም እንዲህ በሉ፡-

ኢማማችንና መሪያችን አሚረል ሙዕሚኒን ዓሊንና ከርስዎና ከርሱ አብራክ የሆኑትን ኢማሞች አስመልክቶ ከርስዎና ከኛ ጌታ ከሆነው አላህ ያደረሰከንን መልዕክት ሰምተን፣ ወደን ተቀብለን፣ እጅ ሰጥተን ታዘናል፡፡ በልቦቻተን፣ በነፍሶቻችን፣ በምላሶቻችነና በእጆቻችን ቃለ መሀላ በማድረግ ምስክርነታችን እንሰጣለን፡፡ በዚህ ቃላችን ላይ እንኖራለን፣ እንምታለን፣ እንቀሰቀሳለን፡፡ መሐላችንን አንቀይርም፣ ሌላ ተተኪም አንፈልግም፣ አንጠራጠርም፣ አንክድም፣ አናወላውልም፣ ቃላችንን አናጥፍም፣ ቃል ኪዳናችንንም አናፈርስም፡፡

አሚሩል ሙዕሚኒኒ ዓሊን እንዲሁም ከርስዎ ቤተሰብ የሆኑትንና ከዓሊ አብራክ የተገኙትን ሐሰንና ሁሴንን እንዲሁም ከነርሱ ቀጥሎ የሚመጡትን የተነገሩንን ኢማሞች አስመልክቶ ያደረሱን መልዕክት ከአላህ የሆነ መልዕክት መሆኑን እንመሰክራለን፡፡ ለነርሱ የገባነው ቃልና የሰጠነው ምስክርነት ከልቦቻችን፣ ከነፍሶቻችን፣ ከምላሶቻችን፣ ከአዕምሮአችን፣ ከእጆቻችንና ከአካላችን በሙሉ የተወሰደ ነው፡፡ በእጅ ማድረግ ባንችልም በምላስ አረጋግጠናል፡፡ በሌላ በማንም አንለውጥም፣ ቃላችንን አናጥፍም፡፡ ልጆቻችንንና ዘመዶቻችንን ጨምሮ ቅርብ ላሉት ሰዎችም ሆነ ሩቅ ላሉት ሁሉ መልዕክቱን እናደርሳለን፡፡

በዚህ ላይ ጌታችን አላህ መስካሪ ይሆን ዘንድ እንለምናለን፡፡ የአላህና የመልዕክተኛው ምስክርነት ምንኛ በቂና ያማረ ነው!”

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እነዚህን ቃላት ልክ እንደጨረሱ፣ ህዝቡ ደግመው አሰሙ፡፡ ተቀባብለው ቃላቸውን ሰጡ፡፡ በዚህ ሁኔታ ለዓሊ ህዝባዊ የድምጽ አሰጣጥ ሥርዓቱ ተጠናቀቀ፡፡ ከዚያም ልክ ኹጥባው ከተጠናቀቀ በኋላ ህዝቡ እጅ በመጨባበጥ ቃል ኪዳናቸውን በተግባር እንዲያረጋግጡ ተደረገ፡፡

## *በገዲር ኹጥባ ነብዩ ያስተላለፉት መልዕክት በጥቅሉ ሲታይ*

ገዲር ላይ በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የተደረገው ህዝባዊ ንግግር (ኹጥባ) በአሥራ አንድ ምዕራፎች ተከፍሎ ሊታይ ይችላል፡፡

በመጀመሪያው ምዕራፍ ውስጥ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አላህን በማመስገን፣ በማወደስ፣ ኃያልነቱን በመዘከር፣ በባህሪያቱና በስሞቹ በማስታወስ፣ ወደር የለሽነቱን በመመስከርና የምህረቱን ስፋት በማድነቅ ይጀምራሉ፡፡ ከዚህ በኋላ ለአላህ አንድነትና ብቸኝነቱ፣ ወደር የለሽነቱና ኃያልነቱ የምስክር ቃል በመስጠት ይቀጥላሉ፡፡

በሁለተኛው ምዕራፍ ውሰጥ ቀጥታ ወደ ዋናው ርዕስ ይሸጋገራሉ፡፡ ዓሊ ኢብን አጢ ጧሊብን አስመልክቶ እጅግ አስፈላጊና አንገብጋቢ ጉዳይ መናገር እንዳለባቸው በመጥቀስ፡- “ዓሊን አስመልክቶ ከአላህ የመጣውን መልዕክት

ካላደረስኩኝ አላህ የጣለብኝን ተልዕኮ እንደልፈጸምኩ ሁኜ እቆጠራለሁ" በማለት የጉባዔውን ርእሰ ጉዳይ ይጀምራሉ፡፡

በሶስተኛው ምዕራፍ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ተተኪያቸው ስለሚሆኑት የአሥራ ሁለቱን ኢማሞች ኢማምነት በማወጅ ሊከሰት የሚችል ማንኛውንም የስልጣን ሽኩቻ ከጅማሬው የሚቀጭ መልዕክት ያስተላልፋሉ፡፡

ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ኹጥባ አንገብጋቢና ወቅታዊ ርዕስ ጉዳዮች አንዱ በህዝቡ ላይ የተሾሙ ኢማሞች በማንኛውም ጊዜና ቦታ በሁሉም ህዝቦች ላይ ያላቸውን የመሪነት ስልጣን አስመልክቶ ያስቀመጡት መመሪያ ነው፡፡ በተጨማሪም እነዚህ ኢማሞች ሐራም (የተከለከሉና ህገ ወጥ ተግባራትና ቃላት) እና ሀላል (የተፈቀዱና የሚበረታቱ ተግባራትና ቃላት) የሆኑትን ጉዳዮች የመወሰን፣ የመፍረድና የመለየት ስልጣንና ዕውቀትን አስመልክቶ የአላህና ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ፍጹም ተወካዮች እንደሆኑ በአጽንኦት የተናገሩበት ሁኔታ ነበር የነበረው፡፡

በአራተኛው ምዕራፍ ውስጥ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የዓሊን እጅ በመያዝና ከፍ በማድረግ ከፍ ባለ ድምጽ እንዲህ በማለት ይናገራሉ፡- "እኔ ወሊይ (መሪ/አዛዥ) የሆንኩት ማንኛውም ሰው ሁሉ፣ እነሆ ይህ ዓሊም ወሊዩ (መሪው/አዛዡ መሆን) አለበት፡፡ አላህ ሆይ! እሱን የሚደግፍን ሁሉ ደግፈው፣ እሱን የሚቃረንን ተቃረነው፣ ለረዳቶቹ ድልን አጐናጽፍ፣ እሱን በሚያስቆጡት ላይ ቁጣህ ይውረድባቸው፡፡"

ከዚያም ሐይማኖቱ ወደ ፍጹምነት/ምሉዕነት ደረጃ የመዳረሱና የአላህ ፀጋና በረከት የማሟላቱ ምስጢር በሌላ ሳይሆን በአሥራ ሁለቱ እንከን የለሽ

ኢማሞች የኢማምነት (መሪነት) ሹመት መሆኑን ያበስራሉ፡፡ በመጨረሻም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የታዘዙትን ነገር በታዘዙት መሠረት መልዕክቱን ማድረሳቸውን አላህ፣ መላኢኮችና ሰዎች ይመሰክሩ ዘንድ ይጠይቃሉ፡፡

በአምስተኛው ምዕራፍ ውስጥ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) "እሱንና ልጆቹ የሆኑትን ተተኪዎቹን እስከ ትንሳዔ ቀንና በአላህ ፊት የመቆሚያ ቀን ድረስ የማይቀበሉ ሰዎች፣ እነዛ ሥራዎቻቸው በዚህ ዓለምም ሆነ በወዲያኛው ዓለም ከንቱ ተደርጎ የሚቆጠር፣ እንዲሁም በጀሃነም እሳት ውስጥ ለዘለዓለም የሚዘወትሩ ናቸው፡፡ ስቃያቸው አይወገድላቸው፡፡ ለጥቂት ጊዜም ቢሆን እፎይታ አያገኙም" በማለት በግልጽ ተናግረዋል፡፡ ከዚያም በርካታ የዓሊን ገድሎችና ትሩፋቶች በዝርዝር ያስታውሳሉ፡፡

በስድስተኛው መዕራፍ ውስጥ ደግሞ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የህዝቡን ትኩረት ወደ መለኮታዊ ቁጣና ቅጣት በመሳብ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ተናገሩ፡፡ ስለቅጣትና አሳማሚ ገጽታዎች የሚያወሳውን የቁርአን አንቀጽ ከቀሩ በኋላ የሚከተለውን የናገራሉ፡-

"በአላህ እምላለሁ! ይህ የቁርአን አንቀጽ የሚናገረው ስለ ማንም ሳይሆን በስም የማውቃቸው፣ የዘር ሐረጋቸውን መቁጠር የምችል ሰሃቦቼ የሆኑ ስለ አንድ ቡድን ነው፡፡ ነገር ግን ማንነታቸውን ሳልጠቅስ ንቄ እንዳልፋቸው ትዕዛዝ ተሰጥቶኛል፡፡ ኃያሉና የላቀው አላህ አፈንጋጮችን፣ የስልጣን ጥመኞችን፣ የተሳሳቱትን፣ ከሀዲዎችን፣ ሙሰኞችንና ዋልጌዎችን ከህዝቡ መካከል ለይተን እናውቅ ዘንድ አንጠሮ ያወጣንና የመረጠን ሁጃዎች (ዋቢዎች) ነን፡፡"

ከዚያም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ወደ እሳት የሚጣሩ መሪዎችን አስመልክቶ አስጠነቀቁ፡፡ “አላህና እኔ ከእንዲህ ዓይነቶቹ ሰዎች የጠራን ነን፡፡” በማለት ስለ “ሴረኞች” (ነብዩን ለመግደል ስላሴሩት ሰዎች) እና “ባለ መዝገቦቹ” (ሴራቸውን በጽሁፍ አዘጋጅተው ድጋፍ ለመሰብሰብ ስለሞከሩት) ቅኔያዊ በሆነ መልኩ አጋለጡ፡፡ እነዚህን ሴረኞችና አሻጥረኞች አስመልክቶ ወደ ኋላ ላይ ዝርዝር መረጃ ይሰጣል፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ኢማማህ (መሪነት) በተረገሙ ሰዎች ሴራ ተጽዕኖ እንደሚያጋጥመው ያስታውቃሉ፡፡

በሰባተኛው ምዕራፍ ውሰጥ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በመለኮታዊ ትዕዛዝ ለተመረጡት ኢማሞች (መሪዎች) ታማኝ መሆንና አህለል ቤይትን መውደድና ማጥበቅ ያለውን ትሩፋትና አስፈላጊነት በአጽንኦት ያስታውቃሉ፡፡ ሱራህ አል ፋቲሃ ከቀሩ በኋላ፡- “ይህ ሱራ ስለነሱ (ስለ ነብዩ ቤተሰቦች/አህለል ቤይት) የሚያወሳ ነው፡፡ በአላህ እምላለሁ! በዚህ ሱራ ውስጥ “ቀጥተኛውን መንገድ የተከተሉና የእውነቱ መንገድ ባለቤት የሆኑት” ተብለው የተጠቀሱት የዓሊ ኢብን አቢ ጧሊብ ተከታዮች ናቸው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በሱራው ውስጥ የተጠቀሱት “አፈንጋጮችና እርጉማን” የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ቤተሰብ (አህለል ቤይት) ጠላቶች ናቸው” በማለት ይናገራሉ፡፡

ስለጀነት ሰዎች የሚያወሱ በርካታ የቁርአን አንቀጾችንም ከቀሩ በኋላ አንቀጾቹ ስለ አህለል ቤይት (የነብዩ ቤተሰቦች) ተከታዮች መሆኑን ገለጹ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የጀሀነም ሰዎች የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጠላቶች መሆናቸውን ያስታውቃሉ፡፡

በስምንተኛው ምዕራፍ ውስጥ ደግሞ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ታላቁን በቂየቱላህ አል-መህዲን (ነፍሶቻችን ቤዛ ይሁኑለትና!) አስመልክቶ ወሳኝ ነጥቦችን በማንሳት ይናገራሉ፡፡ ስለ አል-መህዲ ማንነትና የግል ባህሪያት በመጥቀስ በአል-መህዲ አማካይነት ወደፊት የሚሰፍነውን ፍትህና መልካም ጊዜ በማስታወስ ለአማኞችን ጥሩ ዜና ያበስራሉ፡፡

በዘጠነኛው ምዕራፍ ውስጥ ቅዱሱ ነብይ (ሰ.ዐ.ወ)፡- "ይህንን ንግግር ካበቃሁ በኋላ ወደፊት መጥታችሁ ለዓሊ ቃል መግባታችሁን ለማረጋገጥ ከእኔ ጋር እጅ እንድትጨባበጡ እጠይቃችኋለሁ፡፡ ከዚያም ከሱ (ዓሊ) ጋር ትጨባበጣላችሁ፡፡"

"እነሆ እኔ ለአላህ ቀል በመግባት መሀላ ፈጽሜያለሁ፡፡ ዓሊ ደግሞ ለእኔ ቃል በመግባት መሃላ ፈጽሟል፡፡ እናንተ ደግሞ ለዓሊ ቃል በመግባት መሃላ እንድትፈጽሙ አዛችኋለሁ፡፡ ይህ የአላህ ኢማማህ ነው፡፡"

በአሥረኛው ምዕራፍ ውስጥ ደግሞ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ስለ ኢስላማዊ ህግጋት ያወሳሉ፡፡ ከዚያም የሚከተለውን ይናገራሉ፡-

"ህጋዊ (የተፋቀዱ) ነገሮችንና ህገ ወጥ (የተከለከሉ) ነገሮችን ለመዘርዘርና ለመቁጠር እጅግ ብዙ ስለሆኑ አሁን ያለንበት ሁኔታ አያመቸንም፡፡ ነገር ግን ዓሊን በተመለከተ፣ እንዲሁም ከኔና ከርሱ የአብራክ ክፋይ የሆኑትን ተተኪ ኢማሞችን (መሪዎች) አስመልክቶ ከኃያሉ አላህ ያመጣሁትን መልዕክት መቀበላችሁን የመስክር ቃላችሁን ትሰጡ ዘንድ፣ ቃል ኪዳናችሁን እንድቀበልና ይህንኑን እጅ በመጨባበጥ በተግባር እንድታሳዩ እንዳደርግ ታዝዣለሁ፡፡ ኢማምነታቸው አላህ በፈቀደውና በወሰነው ጊዜ በኢማም አል-መህዲ

አስኪጠናቀቅ ድረስ ይቀጥላል፡፡ በመልካም ነገር የማዘዝ (አል አምር ቢል መዕሩፍ) ቁንጮ ተግባር የሚገለጸው ቃሌን በማስጠበቅ ወደ በጐ ተግባር መምሪትና ከቃሌ የሚያፈነግጡትን በማስታወስ ከእኩይ ተግባር መከልከል ነው፡፡"

በዚህ መልኩ ኢስላማዊ ህግጋቱን አስመልክቶ ለሚነሱ ጥያቄዎች ምላሽ የሚያገኙበትን መዋቅር ይጠቁማሉ፡፡

በመጨረሻው ምዕራፍ ውስጥ ደግሞ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ህዝባዊ ንግግራቸውን ያጠቃልላሉ፡፡ በዚህ መሠረት ከህዝቡ ግልጽ የምስክርነት ቃል በመቀበል ያጠናቅቃሉ፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በመጨረሻ እንዲህ ይላሉ፡- "ዓሊን በተመለከተ የተሰጠውን ውሳኔ መቀበላችሁን ለማረጋገጥ ቃላችሁን ከአንደበታችሁ እንድቀበል በኃያሉና በተከበረው አላህ ታዝዣለሁ፡"

ይህን እንዳሉ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ህዝቡ ምን ማለት እንዳለበት ገለጻ ይሰጣሉ፡፡

አሥራ ሁለቱን ኢማሞች ስለመቀበላቸው፣ በተወሰነው ውሳኔ ላይ ምንም ለውጥ ላያደርጉና ቃላቸውን ላያጥፉ፣ የነብዩን መልዕክት ላልሰሙ ሰዎችና ለቀጣዩ ትውልድ ማስተላለፍ፣ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለአማኞቹ ደህንነት ዱአዕ በማድረግና በመልካሙን ሁሉ በመመኘት፣ መመሪያቸውን (የነብዩን) የሚጥሉትና የሚክዱት ሰዎች ላይ እርግማን እንዲወርድ በመለመን ኹጥባቸውን ያገባድዳሉ፡፡

የህዝባዊ ንግግሩ (ኹጥባው) የመጨረሻ የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ቃል "አልሐምዱ ሊላሂ ረቢል ዓለሚን" (ምስጋና ለዓለማት ጌታ ለሆነው ለአላህ ነው) የሚል ነው።

## *ከኹጥባው ቀጥሎ የነበሩ ሥኑ ሥርዓቶች*

የቅዱሱ ነብይ (ሰ.ዐ.ወ) ታሪካዊ መልዕክት ህዝባዊ ንግግሩን በማድረግ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን ከኹጠባው ሥነ-ሥርዓት በኃላ ይህ ቅዱስ ንግግራቸው ፍጹም እንዳይረሳና እንዳይዘነጋ ለማድረግ ሌሎች ተጨማሪ አጠናካሪ ሥነ ሥርዓቶች እንዲደረጉ አደረጉ።

## *የወንዶች ድምጽ አሰጣጥ (በይዓ አደራረግ) ሥርዓት*

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ኹጥባቸውን ልክ እንዳበቁ ህዝቡ በአንድነት በመጮህ፡- "ከአላህና ከመልዕክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) የደረሰንን ጉዳይ ሰምተንና ተቀብለን በልቦቻችን፣ በምላሶቻችንና በእጆቻችን የምስክርነት ቃላችንን ሰጥተናል" በማለት ተናገሩ።

በዚህ ሁኔታ ሰዎች በቡድን በቡድን ሆነው ወደ ነብዩና ዓሊ በመሄድ የእጅ መጨባበጥና የእንኳን ደስ አላችሁ መልዕክት ማስተላለፍ ሥርዓት ተካሄደ።

በኹጥባው ወቅት ነብዩ ቀደም ሲል ህዝቡ ለዚህ ተግባር እንዲዘጋጁ ማስታወሳቸው ተጠቅሷል።

እንዲህ በማለት ነበር ቀድመው ያስታወቁት፡-

“ይህንን ንግግር ከበቃሁ በኋላ ወደ ፊት መጥታችሁ ለዓሊ ቃል መግባታችሁን በማረጋገጥ ከእኔ ጋር እጅ እንድትጨባበጡ እጠይቃችኋለሁ፡፡ ከዚያ ደግሞ ከርሱ ጋር (ከዓሊይ ጋር) ትጨባበጣላችሁ፡፡”

ከዚያ በኋላ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የዚህ በይዓ (ቃል-ኪዳን መግባት) ጉዳይ አስፈላጊውን ትኩረት ማግኘቱን፣ በማያዳግም ሁኔታ መገለጹንና መለኮታዊ ቦታ መያዙን አበክረው አረጋገጡ፡፡

“እነሆ እኔ ለአላህ ቃል በመግባት የምስክርነት ቃሌን በመሃላ ፈጽሜያለሁ፡፡ ዓሊ ደግሞ ለኔ ቃል በመግባት የምስክርነት ቃሉ በመሃላ ፈጽሟል፡፡ እናንተም ዓሊ አላህ የተካው መሆኑን ሰምታችሁ መቀበላችሁን ቃል በመግባት የምስክርነት ቃላችሁን በመሃላ እንድትፈጽሙ እመራችኋለሁ” በማለት ተናገሩ፡፡ ከዚያም የሚከተለውን የቁርአን አንቀጽ ቀሩ፡-

“እነዛ በዛፉ ሥር ከአንተ ጋር ቃል ኪዳን የገቡ ሰዎች፣ በእርግጥ ቃል እየገቡ ያሉት ከአላህ ጋር ነው፡፡ የአላህ እጅ ከእጆቻቸው በላይ ነው. . . ”፡፡

ልክ የኹጥባ ሥርዓቱ እንዳበቃ ሁለት ድንኳኖች እንዲተከሉ አዘዙ፡፡ አንድ ድንኳን ለርሳቸው አንዱ ደግሞ ለዓሊ፡፡

ሰዎች በቡድን በቡድን እየሆኑ የዓሊን ኢማምነትና የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ተተኪ መሆኑን መቀበላቸውንና ቃል መስጠታቸውን በተግባር ለማረጋገጥ፣ ወደ ዓሊ ድንኳን ከመሄዳቸው በፊት ወደ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ድንኳን በመሄድ በይዓ

አደረጉ፡፡ ሰዎች ወደሳቸው እየጐረፉ የመጨባበጡ ሥርዓት እየተካሄደ እያለ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለህዝቡ እንዲህ ይሉ ነበር፡-

“እንኳን ደስ አለህ በሉኝ፡፡ አላህ የነብይነትን ቦታ መርጦ ለኔ ሰጠኝ፡፡ ኢማምነትን (መሪነትን) ደግሞ ለቤተዘሮቼ (አህለል ቤይቶቼ) አጐናጸፈ፡፡”

ይህ ሥነ-ሥርዓት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በገዲር ኹም ቆይታ ባደረጉበት በነዛ ሶስት ቀናት ውስጥ ተጠናቀቀ፡፡

እዚህ ላይ መነሳት ያለበት በግልጽ የታየ ነገር ቢኖር ለዓሊይ ቃል በመግባቱ (በይዳ በማድረጉና የእንኳን ደስ አላህ መልዕክት በማስተላለፍ) ቀዳሚውን ቦታ የወሰዱት ሰዎች ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ካለፉ በኋላ ቃላቸውን በማጠፍና ቃል ኪዳናቸውን በማፍረስ የመጀመሪያውን እርምጃ የወሰዱትም እነዚሁ ሰዎች ነበሩ፡፡

ጉዳዩ በአላህ የታዘዘ ስለመሆኑ ወይም ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ፍላጐት ብቻ የመነጨ ስለመሆኑ አጥብቀው ጠይቀውም ነበር፡፡ ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) ከአላህ የመጣ ትዕዛዝ መሆኑን አስረግጠው ነግረዋቸው ነበር፡፡

ኡመር በይዓ ካደረገ በኋላ ለዓሊ እንዲህ ብሏል፡- “መልካም --- መልካም! እነሆ የኔና የሁሉም ወንድና ሴት አማኞች ወሊይ (መሪ/አዛዥ) ለመሆን በቅተሃል!”

## *የሴቶች ድምጽ አሰጣጥ (በይዓ አደራረግ) ሥርዓት*

በሌላው በኩል ደግሞ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በውኃ የተሞላ ዕቃ እንዲቀርብ አዘዙ፡፡ ከዚያም ዕቃውን በመጋረጃ በመከለል ሁለት ቦታ እንዲከፈል አደረጉ፡፡ ዓሊ በአንደኛው ክፍል ውስጥ እጁን ሲነክር ሴቶች ደግሞ ሌላኛው ክፍል ውስጥ እጆቻቸውን ይነክራሉ፡፡ በዚህ መልኩ የሴቶች በይዓ አደራረግ ሥርዓት ተከናወነ፡፡ በገዲር ኹም የተካፈለ ለዓሊይ በይዓ ከማድረግ ያመለጠ ማንም ሰው ሊኖር አይችልም፡፡ በገዲር ላይ ተገኝቶ በይዓ ሳያደርግ ቀረሁ ብሎ የሚናገር ሰውም ሊገኝ አይችልም፡፡

በዚህ አጋጣሚ ቅድስት ፋጢማ (ዐ.ሰ)ና የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ባለቤቶች (ሚስቶች) በሙሉ የዚህ ሥነ ሥርዓት ተካፋይ እንደነበሩ መጥቀሱ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

## *የነብዩ ጥምጣም*

በሥነ ሥርዓቱ ወቅት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ‘ሰሃብ’ በመባል የሚጠራውን ጥምጣማቸውን በዓሊ ራስ ላይ በማድረግ የጥምጣሙ ዘርፍ በደረቱ ላይ እንዲንጠለጠል አደረጉ፡፡ በዚሁ ወቅት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ አሉ፡- “ኃያሉ አላህ በበድርና በሁነይን ጦርነት ወቅት ይህንን ጥምጣም በጠመጠሙ መላኢካዎች አማካኝነት ድጋፍ ሰጥቶናል፡፡” በተጨማሪም ጥምጣም የአረቦች የሹመት መግለጫ ምልክት መሆኑን አበክረው ተናገሩ፡፡

ይህ ደግሞ የሚያመለክተው ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለዓሊና እንከን የለሽ ልጆቹ ዘለዓለማዊ ኩራት ማጐናጸፋቸውንና የመሪነቱ ቦታ ለነርሱ ብቻ እንደሚገባ ማረጋገጣቸውን ነው፡፡

### *የገዲር ግጥም*

በዚህ ሥነ ሥርዓት ወቅት ገጣሚው ሐሳን ኢብን ሳቢት፣ ዓሊ የነብዩ ተተኪና መሪ ተደርጎ የተሾመበትን ክስተት አስመልክቶ በወቅቱ የቋረጠውን ስንኝ (የገጠመውን ግጥም) ያቀርብ ዘንድ ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ፈቃደ ጠየቀ፣፡ እሳቸውም "በል አቅርብ፣ አላህ በረካ ያድርግልህ" በማለት ፈቀዱለት፡፡

ከዚያም ሐሳን "የቁሬይሽ ታላላቅ ሰዎች ሆይ! በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዕውቀና አግኝቶ እንዳቀርብ የተፈቀደልኝን ግጥሜን ስሙ" በማለት ጀመረ፡-

ቅዱሱን ነብይ አላያችሁም ወይ
በገዲር በረሃ ከፍ ባለው መድረክ ላይ
አዋጅ ሲናገሩ በጠራራ ፀሐይ

የመጨረሻው መልዕክት የዲን መደምደሚያ
የምሉዕነት ምንጭ ጥብቅ ማሳሰቢያ
ከኃያሉ አላህ ከሰማይ ሰማያት
ጂብሪል ይዞ መጣ አንገብጋቢ መልዕክት

እነሆ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ያድርሱ መልዕክቱን
ከጌታ የመጣ ጥብቅ ትዕዛዛቱን

ከአጥናፍ እስከ አጥናፍ አዋጅ ይናገሩ
ጠባቂው አላህ ነው ማንንም አይፍሩ

ይህንን የአላህ መልዕክት ካልተናገሩማ
የእስከ ዛሬው ልፋት አልሆነም ፍሬያማ

ይህ ጥብቅ ትዕዛዝ ለህዝቡ ካልደረሰ
መላው ተልዕኮዎ በከንቱ ፈረሰ
በሉ ይናገሩ አዋጁን ይንገሩ
ጠባቂው አላህ ነው ማንም አይፍሩ

ቅዱሱ ነብይም መድረኩ ላይ ወጥተው
ወንድማቸው ዓሊን በቀኝ አቁመው
በቀኝ እጃቸው እጁን ከፍ አድርገው
ገዲር አደባባይ በሺዎች ፊት ቆመው
"እኔ ወሊይ (መሪ) የሆንኩት ሁሉም ሰው
እነሆ ይህ ዓሊም ወሊዩ (መሪው) ነው

ልብ ያለው ልብ ይበል ይስማ ጆሮ ያለው
ከኔ በኋላ መሪያችሁ እሱ ነው
ልብ ያለው ልብ ይበል ጆሮ ያለው ይስማ
በአላህ ውሳኔ ማንም አያቅማማ

አላህ ሆይ!
እሱን (ዓሊን) ለተወዳጅ ወዳጅ ሁነው
እሱን የሚጠላን ተጣላው
ለደጋፊዎቹ ድል አብስር
የጠላቶቹን አከርካሪ ስበር

እንደ ሙሉ ጨረቃ ወደ ብርሃን ለሚመራ
ጨለማን ገርስሶ ወደ እውነት ለሚጣራ
ለደጋፊዎቹና ለወዳጆቹ መከታ ሁንላቸው
የድል ባለቤት ይሁኑ በለስ ይቅናቸው

አላህ ሆይ!
የሚየስቆጡትን ተቆጣቸው
በፍርዱም ቀን ተፋረዳቸው

ይህ በገዲር የግጥም ታሪክ ውስጥ ፈር ቀዳጁ ነው፡፡ ባለፍት አሥራ አራት ምዕተ-ዓመታት ውስጥ የገዲርን ክስተት ለመዘክርና ህያው ሆኖ እንዲቆይ ለማድረግ ገጣሚዎች ዘመን የማይሽራቸው በርካታ ግጥመችን ገጥመዋል፣ ስንኝ ቋጥረዋል፣ ቅኔ ተቀኝተዋል፡፡

## ጂብሪል (ገብርኤል) በገዲር

ሰዎችን ጥርጣሬና ክርክር ከሥሩ መንግሎ ያጠፋ ሌላ ክስተትም ነበር፡፡ አንድ መልከ መልካም ሰው ህዝቡ ውስጥ ቆሞ ሲናገር ሰዎቹ ሁሉ ያዩ ነበር፡፡ ይህ

መልከ መልካም ሰው እንዲህ ይል ነበር፡- “ይህ ነብይ ለዚህ ሰው ያሰረውን ቃል ኪዳን በአላህ የካደ (የከፈረ) ሰው ካልሆነ በስተቀር ማንም ሰው አይፈታም (አያፈርስም)፡፡” ዑመር ወደ ሰውየው መጣና ማንነቱን ጠየቀ፡፡ ነገር ግን ምንም ምላሽ አላገኘም፡፡

ከዚያም ወደ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መጣና ስላየው ነገር ነገራቸው፡፡ ነብዩም እንዲህ አሉት፡- “ያየኸው መላዕካ (መልዓኩ) ጂብሪል (ገብርኤል) ነበር፡፡ ይህንን እስር (ቃልኪዳን) እንዳትዘነጋውና እንዳትፈታው (እንዳታፈርሰው) አስጠነቅቅሃለሁ፡፡”

## *የገዲር ተዓምር*

የገዲር መለኮታዊ ክስተት ተዓምራዊ ነበር፡፡ በሥነ ሥርዓቱ መደምደሚያ አካባቢ፣ በሶስተኛው ቀን ከሙናፊቆች የሆነ አል-ሀሪስ አል-ፊህሪ የሚባል ሰው እንዲህ ሲል ተናገረ፡- “አላህ ሆይ! በእርግጥ ይህ ጉዳይ ከአንተ የመጣ ትዕዛዝ ከሆነ ከሰማይ ድንጋይ አውርድብን ወይም ደግሞ የሆነ አይቀጡ ቅጣት ቅጣን፡፡”

ይህን ተናግሮ እንዳበቃ አላህ ከሰማይ ድንጋይ አውርዶበት ድንጋዩ በጭንቅላቱ ገብቶ በመቀመጫው ወጣ፡፡ ወዲያው ሞተ፡፡ ይህን በማስመልከት አላህ የቁርአን አንቀጾች አወረደ፡፡ እነዚህ አንቀጾችም በሱራህ አል-መዓሪጅ ውስጥ ይገኛሉ፡፡

በዚህ ተዓምር የተነሳ እያንዳንዱ የገዲር እድምተኛ ውሳኔውና ትዕዛዙ የመጣው ከአላህ መሆኑን ያለጥርጥር ያረጋገጠበት ሁኔታ ነበር የበረው፡፡ በተጨማሪም

ጉዳዩ መለኮታዊ ውሳኔ መሆኑንና አላህ ምንጊዜም ይህንን ውሳኔውን እንደሚጠብቅ፣ እንደሚከላከልና እንደሚያፀና ያረጋገጡበት ክስተት ነበር፡፡

ከዚህ ክስተት በኋላ ቅዱሱ ነብይ (ሰ.ዐ.ወ) ለህዝቡ ሲናገሩ፡- "የሆነውን አይታችኋል፣ አይደለም እንዴ" ብለው ጠየቁ፡፡ ህዝቡም፡- "አዎ! አይተናል" ብለወ መለሱ፡፡

ከዚያም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ቀጠል አድርገው፡- "ለተከታዮቹ መልካም ብስራትን አበስራለሁ፡፡ ደስ ይበላችሁ! ለአፈንጋጮችና ለተቃዋሚዎች ወየውላቸው! ዓሊና ደጋፊዎቹ (ወዳጆቹ) እንደ ሙሽሮች ሆነው ወደ ጀነት ይወሰዳሉ፡፡ ለግላጋ ወጣቶች ሆነው፣ ተሸላልመውና ዘውድ ደፍተው፣ በክብር ዘወትር ይኖራሉ፣፡ ፍራቻ የሚባል አያገኛቸውም፡፡ ወሰንና ወደር የለሽ ፍጹም ደስታን ይጐናጸፋሉ፡፡ የአላህ ውዴታን ያገኛሉ፡፡ ይህ አምሳያ የሌለው ድል ይሆናል፡፡ የዓለማት ጌታ የሆነው ጌታቸው ዘንድ በተለየ ቅዱስ ቦታ ይኖራሉ፡፡ ያሻቸውን ሁሉ ለዘለዓለም ያገኛሉ፡፡ መላኢካዎች (መላዕክቶች) ሠላምታ ያቀርቡላቸዋል፡- 'ሰላም ለናንተ ይሁን! ለትዕግስታችሁና ለጥንካሬያችሁ (ሰላም ለናንተ ይሁን!) በሥራችሁ ውጤት ደስ ይበላችሁ! ተደሰቱ! "

## *የኢስላም ኃይማኖት ገዲር ላይ ፍጹምና ምሉዕ ሆነ*

በዕለተ ገዲር ሙስሊሞች ለዘመናት የሚያነቡትን የቁርአን አንቀጽ፣ በሙስሊሞች ታሪክ ውስጥ ይህ ታላቅ ቀን እንዳይረሳና ዝንተ ዓለም እየተወሳ ይኖር ዘንድ አላህ የቁርአን አንቀ አወረደ፡፡ ይህ ቀን አላህ ኃይማኖቱን ፍጹም ያደረገበትና ፀጋውን ያሟላበት ታላቅ ዕለት ነው፡፡ ከዚያን ዕለት ጀምሮ

ከሃዲዎች ተስፋ ቆረጡ፡፡ ይህንን ቅዱስ ኃይማኖት ለመጋፈጥ ወሽመጣቸው ተሰበረ፡፡ የሚቀጥለው የቁርአን አንቀጽ መዲና ከወረደ ሱራህ (ምዕራፍ) የተወሰደ ነው፡፡

አላህ እንዲህ ይላል፡-

***እነዚያ የካዱት፣ ከሃይማኖታችሁ ተስፋ ቆረጡ፤ ስለዚህ አትፍሯቸው፤ ፍሩኝም፤ ዛሬ ሃይማኖታችሁን ለናንተ ሞላሁላችሁ፡፡ ጸጋዬንም በናንተ ላይ ፈጸምኩ፡፡ ለናንተም እስላምን ከሃይማኖት በኩል ወደድኩ፡፡ (5፡3)***

በእርግጥ ይህ ለከሃዲዎች (ኢ-አማንያን) ተስፋ የሚያስቆርጥና የሚቆጭ ነገር ነው፡፡ ኃይማኖቱን ጠብቀው ህዝቡን ወደ እውነት የሚመሩ፣ የግለሰብንም ሆነ የህብረተሰቡን እምነት ወደ ትክከለኛው መንገድ የሚያቀኑና የህዝቡን ሁለመና ህይወት የሚመሩት መሪዎች ሲመረጡና ሲሾሙ በማየታቸው አንጀታቸው አሯል፡፡ ከህዲዎቹ ይህ ሃይማኖት እስከ መጨረሻው ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) በሚተኩ መሪዎች መመራቱ እንደማይበጃቸው ጠንቅቀው ስላወቁ አንገበገባቸው፡፡ ልክ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በሄዱበት መንገድ ሄደው፣ ፈለጋቸውን ተከትለው ለመላው ሙስሊም የሚሰሩ ከሆነ አፈንጋጮችና ከሃዲዎች ኃይማኖቱን መበረዝ እንደማይችሉና ህዝቡን ማጥመም እንደማይሆንላቸው ያለጥርጥር መናገር ይቻላል፡፡

በዚህ መልኩ አላህ ኃይማኖቱን ፍጹምና ምሉዕ በማድረግና ፀጋውንም ለአማኞቹ በማሟላት፣ ከሃዲዎች ይህንን ኃይማኖት ለመጋፈጥና ለመቃወም ተስፋ የሚየስቆርጥ ፖሊሲ በመቅረጽ ለቀጣዩ ትውልድ መንገዱን ጠርጐ አመቻቸ፡፡ እንዲሁም ከዚህ እውነተኛ መንገድ የነብዩ መሐመድና የእንከን የለሾቹ ቤተዘራቸው (አህለል ቤይታቸው) መንገድ ያፈነገጡ ሰዎች ምንም

ማስተባበያና ማመካኛ እንዳይኖራቸውና በእንዲህ ዓይነቶቹ ሰዎች ላይ ማስረጃ እንዲሆን አደረገ፡፡

## *የገዲር ኹጥባ ሥነ-ሥርዓት መጠናቀቅ*

ከሶስት ቀናት በኋላ የቃለ መሃላ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓቱ ተጠናቀቀ፡፡ እነዚህ ቀናትም ***የቃል ኪዳን ቀናት*** ተብለው ተሰየሙ፡፡ አዲሱን መሪያቸውን (ኢማማቸውን) አስመልክተው የማረጋገጫ ቃላቸውን ከሰጡና ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ከተሰናበቱ በኃላ እያንዳንዱ ጐሳ ወደየ ሀገሩ መመለስ ጀመረ፡፡ ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) ወደ መዲና አቀኑ፡፡ በገዲር የተደረገው ድርጊት በሙሉ ሳይቆይ ዜናው በየከተማውና ገጠሩ ተሰራጨ፡፡ በዚህ መልኩ መልዕክቱ ሁሉም ህዝብ ጋ ደረሰ፡፡ ስለዚህ አላህ በህዝቡ ላይ ማስረጃውን ፍጹም አደረገ፡፡

እነዛ 120 ሺህ እድምተኞች እያንዳንዳቸው የገዲርን ህዝባዊ ንግግር (ኹጥባ) ጠብቀው አቆይተው ለቤተሰቦቻቸው፣ ለዘመዶቻቸውና ለጓደኞቻቸው መተረክ ነበረባቸው፡፡ ነገር ግን ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ካለፉ በኋላ ወዲያው በገዢ ክፍሎች በተፈጠረ ውስብስብና አስቸጋሪ የፖለቲካ ሁኔታዎች የተነሳ ህዝቡ ቀስ በቀስ ያንን ታሪካዊ ንግግር እየረሳ መጣ፡፡

በገዲር የተነገረው አዋጅና የተገባው ቃል ኪዳን የተካሄደው የመሪነቱን ቦታ ያለ አግባብ የወሰዱ ሰዎች ባሉበት መሆን ስለነበረበት እንዲህ ዓይነቱ የስልጣን ሽኩቻ እንዲከሰት መፍቀድ አልነበረባቸውም፡፡ ያንን ታሪክ ለመቀልበስና ለመደበቅ አንዳችም ሙከራ ማድረግ እንደሌለባቸው ግልጽ ነው፡፡

ነገር ግን የገዲርን ክስተት ለቀጣዩ ትውልድ ያስተላለፉ በርካታ ግለሰቦች ግደርጊቶቹንና ሥነ ሥርዓቱን ጠብቀው ለማቆየት ችለዋል፡፡ ይህ ለእውነተኛ ሙስሊሞች እጅግ ወሳኝና አማራጭ የሌለው ጉዳይ በመሆኑ ማዕበሉን ማንም ሊገታው አይችልም፡፡

እላይ ከተጠቀሰው ምክንያት የተነሳ በገዲር የተደረገውን ንግግር ሙሉ ይዘቱንና ዝርዝር ጉዳዩን እንዳለ መተረክ የሚያስችል ዘገባ ላይ መድረስ የማይቻል ነው፡፡ ሙሉ ይዘቱን እንደተጠበቀ ሆኖ መዘገብ ከተቻለው ከዚህ ከአቢይ ጉዳይ ባሻገር ሌሎች የኢስላም ጉዳዮችን ዝርዝር ነገሮች በመያዝም የተለየ ቦታ አለው፡፡ በጣም ታዋቂ የሆኑ የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሐዲስ ተራኪ የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰሃባዎች፣ የተለያየ መዝሀብ (ቡድን)ና አቋም የነበራቸው የነበሩ ቢሆንም እንኳ ይህንን የገዲር ጉዳይ ላለፍት አሥራ አራት ዓመታት ሲተረኩና ሲያስተላልፉ ኖረዋል፡፡

# 2
# ኢብሊሶችና ሙናፊቆች በገዲር

የገዲር ክስተት ለሴራዎችና አሻጥሮች አዲስ ምዕራፍ የከፈተ ክስተት ነው፡፡ የኢስላም ጠላቶች የነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ዕቅድ ለመቀልበስ ብዙ አልመው ነበር፡፡ እነዚህ ሴራዎች የተሞከሩት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ኸሊፎቻቸውን (ተተኪዎቻቸውን) ለይተውና መርጠው ለመጨረሻው ስንብት በተዘጋጁበት በዛው ወቅት ነበር፡፡

ኢብሊሶች ዓላማቸውን ለማሳካት ይኳትኑ ነበር፣ ሙናፊቆችም የነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ግዛት ኢማሞች (መሪዎች) መሪነታቸውን ለመቀልበስና የስልጣን ጥማታቸውን ለማርካት የሚያስችላቸውን ኃይል በመሰባሰብ ተግባር ተጠምደው ነበር፡፡

ቀጥሎ ከዕለተ ገዲር ጀምሮ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከዚህ ዓለም በሞት እስከተለዩበት ጊዜ ባሉት ሁለት ወራት ውስጥ ሙናፊቆች ያሴሩት ሴራዎች በአጭሩ ይቀርባሉ፡፡

## ኢብሊሶች በገዲር

ኢማም ዓሊ ተከታዩ የኢስላም ኢማም (መሪ) ሆነው የተመረጡበትን ያን ደማቅ ሥነ ሥርዓት ሰይጣንና አጋፋሪዎቹ ታድመዋል፡፡ የሰይጣን ጓዶች ለአለቃቸው ሲናገሩ፡- "ይህ የተከሰተው ነገር ከተነገረን በተቃራኒው ነው የሆነው፡፡ እንደነገርከን ከሆነ ይህ ሰው ትቷቸው ከሄደ በኋላ ሰሃቦቹ በሙሉ እንደሚበታተኑና እንደሚለያዩ ነበር፡፡ አሁን ግን የምናየው ነገር በቋሚነት

የተረጋገጠላቸው ነገር ነው፡፡ የዚህ ህዝብ መሪዎች (ኢማሞች) በቅደም ተከተላቸው ተለይተው ተሹመዋል፡፡ እንግዲህ ይኸው ይህ ህዝብ በመለኮታዊ ፈቃድና ጥበቃ ሥር ሆነዋል፡፡ እነዚህ ህዝቦች ከነብዩ በኋላ በአስተማማኝና ታማኝ ኢማሞች መሪነት ሥር የሚቆዩ ከሆነ ደግሞ አንተም ሆነ እኛ በነሱ ላይ የበላይነት የማግኘቱ ጉዳይ አከተመ ማለት ነው፡፡”

“ሂድ ወደዚያ! የዚህ ነብይ ሰሃባዎች ከዚህ ንግግር አንዳችም ቃል በተግባር እንደማያውሉ ቃል ገብተውልኛል” አላቸው የሰይጣኖቹ አለቃ በተደናገጠና ተስፋ በቆረጠ ሁኔታ፡፡

ነብዩ ካለፉ በኋላ ሰዎች ቃል ኪዳናቸውን እንዳፈረሱ ሰይጣን ጓዶቹን ለስብሰባ ጠራ፡፡ በዚህ ጊዜ ጭፍራዎቹ በፊቱ ቆመው ለጥ ብለው እጅ ከነሱ በኋላ፡- “አቤቱ መሪያችን፣ አቤቱ አለቃችን! በእርግጥ አንተ ነህ አደም ከጀት እንዲባረር ያደረከው” በማለት ተናዘዙ፡፡

ከዚያም ሰይጣን፡- “ከነብዩ በኋላ ይህ ህዝብ መንገዱን አይለቅም አላችሁን? በጭራሽ! በነሱ ላይ የበላይነት አይኖረውም ብላችሁ ዘባርቃችሁ ነበር፡፡ እነሆ አሁን የጌታቸውን ትዕዛዝና የነብያቸውን መመሪያ ወደ ጐን እንደተውና በኔ ሥር እንደወደቁ አያችሁ” በማለት በኩራት ተናገረ፡፡

## *ሙናፊቆች በገዲር*

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ኸሊፋቸውን (ተተኪያቸውን) መምረጣቸውን ተከትሎና የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከዚህ ዓለም በሞት መለየትን ሲጠባበቁ የነበሩ ሙናፊቆች እርኩስ ሴራቸውን ለመወጠን የሚንደፋደፉበት ወቅት ነበር፡፡ ዕቅዳቸውን ለመተግበር የነብዩን ህልፈት ይጠባበቁ ነበር፡፡

## *የመጀመሪያው ሴራ*

የሙናፊቆች አባል የሆኑ ሁለት ሰዎች ሚስጥራዊ ግንኙነትና ወዳጅነት ፈጠሩ፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከተገደሉ ወይም ከሞቱ በኋላ ቤተሰቦቻቸው (አህለልቤታቸው) የመሪነቱን ቦታ እንዳይዙ መታገል እንዳለባቸው ቃል ተገባቡ፡፡ ይህ የመጀመያው ሴራ ውጥን ነበር፡፡ በኋላ ሌሎች ሶስት ሰዎች ተጨመሩ፡፡ ይህን የሴራ ዕቅዳቸውን በጽሁፍ ካሳፈሩ በኋላ መዝገቡን ካዕባ (በመካ የሚገኘው የአላህ ቅዱስ ቤት) አጠገብ የሆነ ቦታ ቀበሩት፡፡ ሚስጢራዊ ስብሰባቸውን የሚየደርጉት እዚህ ቦታ ነበር፡፡

የዚህ ሴራ አንደኛው አባል ሲናገር፡- “የኔን ህዝቦች-አንሳሪን (ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) የተቀበሉና የረዱ የመዲና ሰዎች) በተመለከተ በዚህ እቅዳችን ውስጥ ጣልቃ እንዳይገቡ በማድረጉ ሥራ እምነታችሁን ጣሉብኝ፡፡ እናንተም እንደዚሁ የቁሬይሽ ሰዎችን በተመለከተ ዋስትና ልትሰጡን ይገባል” በማለት አስተያየቱን ሰጠ፡፡

የአንሳር አለቃ የነበረው ሰዕድ ቢን ኡባዳ እንዲህ ዓይነት ነገር እንዲከሰት አይፈቅድም፡፡ ስለዚህ በሺር ቢን ሰዕድና ኡሰይድ ቢን ሁዴይር ይህንን ሴራ ለማስፈጸምና የማሳመን ሥራ እንዲሰሩ የታጩ ነበሩ፡፡ እነዚህ ሁለቱ ሰዎች አውስና ኸዝረጅ በሚባሉት በአንሷር ሁለቱ ታላላቅ ቡድኖች ላይ የበላይነትና ተሰሚነት ያላቸው ግለሰቦች ነበሩ፡፡ ስለዚህ በሴራው ላይ እንዲሳተፉ ተደረጉ፡፡

## *ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ለመግደል የተሸረበ ሴራ*

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የመጨረሻውን (የመሰናበቻውን) ሐጅ አጠናቀው ወደ መዲና ለመመለስ በመንገድ ላይ ሳሉ እነዛ አምስቱ ሰዎች ሌሎች ዘጠኝ ሰዎችን

አስከትለው ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ለመግደል አቀዱ፡፡ በአርሻ ተራራ ጫፍ ላይ ሆነው ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) መንገድ ላይ ጠብቀው ለመግደል ይጠባበቁ ነበር፡፡

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ተራራው ጫፍ ላይ ሲደርሱ በተሳፈሩበት ግመል ላይ ትላልቅ ቋጥኞች (ድንጋዮች) በመወርወር ከጣሉዋቸው በኋላ፣ ጨለማውን ተገን በማድረግ ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ከገደሉዋቸው በኋላ አምልጠው ምንም ሳይታወቅባቸው ከህዝቡ ጋር ለመቀላቀል ነበር ዕቅዳቸው፡፡

ኃያሉ አላህ ስለ ሰዎቹ ሴራ ቀድሞ ለነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በመንገር ከጥቃታቸው እንደሚከላከሏቸውም አስታወቋቸው፡፡

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ተራራው ጫፍ ደርሰው በሌላው አቅጣጫ ቁልቁል መንገድ እንደጀመሩ ሙናፊቆቹ ትላልቅ ቋጥኞች ወደ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ግመል ወረወሩ፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ወዲያው ግመላቸውን አቆሙ፡፡

ድንጋዮቹ እየተንከባለሉ ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ርቀው ቁልቁል ወረዱ፡፡ በዚህ ወቅት ሁዘይፋ የግመሉን ገመድ ይዞ ከፊት ሲጐትት አማር ደግሞ ከኋላ እየነዳ ነበር፡፡ ሙናፊቆቹ ሰይፋቸውን ከአፎቱ በመምዘዝ ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ለማጥቃት ሞከሩ፡፡ ሁዘይፋና አማር ገጥሟቸው እንዲፈረጥጡ አደረጓቸው፡፡

ሙናፊቆቹ ፊታቸውን ወደ ቅፍለቱ (የመንገደኞች ጭፍራ) እንዳዞሩ ከትላልቅ ቋጥኞች ኋላ ለመደበቅ ሞከረው ነበር፡፡ ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እጅ የፈለቀ አንጸባራቂ ብርሃን አካባቢውን ለአጭር ጊዜ አበራ፡፡ ሁዘይፋና አማር በቋጥኞቹ ሥር የተደበቁትን እነዛን አሥራ አራቱን ግለሰቦች ለማወቅ ችለው ነበር፡፡

ነገር ግን ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከነዚህ ሙናፊቆች ጋር በዛ ወሳኝ ወቅት ውስጥ ምንም ፍንጭ እንዳይሰጡና ከነሱ ጋር ይፋ የወጣ ቅራኔ ውስጥ እንዳይገቡ ቀደም ብሎ ትዕዛዝ ተሰጥቷቸው ነበር፡፡ ይህም ቀደም ሲል የነበሩ ጥረቶች ከነፋሱ ጋር እንዳይበተኑና ሙናፊቆቹ ግባቸውን እንዳይመቱ ለመከላከል የተደረገ ዘዴ ነው፡፡

## ሁለተኛው ሴራ

በመዲና 34 ዋና ዋና ሙናፊቆች ሌላ ሚስጢራዊ ስብሰባ በማካሄድ ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ህልፈት በኋላ መውሰድ ስላለባቸው እርምጃዎች ላይ መከሩ፡፡ እነዚህ የየጐሳው አለቆችና የአንዳንድ ቡድኖች ኃላፊዎች ነበሩ፡፡

ሴራቸውን በጽሁፍ በማስፈር እያንዳንዳቸው ስማቸውን ጽፈው ተፈራረሙ፡፡ መዝገቡ (ወረቀቱ) ቀደም ሲል በነበረው መዝገብ (ወረቀት) አጠገብ እንዲቀበር (እንዲደበቅ) ለአንደኛው ኃላፊነቱን ሰጡ፡፡

በዚህ መልኩ ሙናፊቆቹ ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ህልፈት በኋላ የመሪነቱን (የኢማምነትን) ጉዳይ አስመልክቶ መሆን ስለሚገባው ሁኔታ ሴራቸውን ጠነሰሱ፡፡ ዕቅዳቸውን በመተግበር ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለሀያ ሶስት ዓመታት ሲገነቡ የነበሩትን ጥረታቸውን ለማውደም በቁ፡፡
ይህን እንጂ የገዲር አንጸባራቂ ብርሃን ይህን ሁሉ ችሎ ዝንተ ዓለም ብርሀኑን ሊሰጥ ቀጠለ፡፡ በአሥራ አምስት ምዕተ ዓመታት ዘመን ውስጥ በአሥራ ሁለቱ ኢማሞች መሪነት ከልብ የሚያምኑና የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ቤተሰብ (አህለል ቤይት) ፍቅር ያደረባቸው በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሙስሊሞች በዓለም ታሪክ ውስጥ

ቁንጮ ቦታ ለመያዝ በቅተዋል፡፡ በመላው ዓለም ውስጥ የተለያዩ ቦታዎችን ለመቆናጠጥ ችለዋል፡፡ ለነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ቤተዘር የታማኝነት ፀሐይ በዓለማችን ላይ እስከ አሁን እየበራ ሲሆን ለወደፊቱ ደግሞ በኢማሞች መደምደሚያ መህዲ እጅ ዓለማችን የበለጠ ፍትህና እኩልነት የሚሰፍንባት የሰላም ምድር የምትሆንበት ዘመን እንደሚመጣ በእርግጠኝነት እንናገራለን፡፡

ቀደም ሲል የገዲር ክስተት፣ ከክስተቱ በፊትና በኋላ የነበሩትን ነገሮች ቀንጭበን ለማሳየት ሞክረናል፡፡ የገዲርን ኹጥባ (ህዝባዊ ንግግር) በሚገባ ለመረዳትና ከመሠረቱ ለማወቅ ቀደም ሲል የተጠቃቀሱ ሁናቴዎችን በአዕምሮ ቀርጾ መያዝ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

## 3

## *የገዲር ኹጥባ ዓላማዎች በአጭሩ*

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በገዲር ኹም ያደረጉት ግልጽ ህዝባዊ ንግግር (ኹጥባ) ዓላማ ለመረዳት ለነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) ሆነ ለእድምተኛው የነበረውን ልዩ ቦታና በወቅቱ የነበረውን ሁኔታ ልብ ማለት ያስፈልጋል፡፡ በወቅቱ የነበሩት እድምተኞች በማንኛውም ዘመን የነበሩትንና ያሉትን መላውን ሙስሊሞች የሚወክሉ ነበሩ፡፡

ስለዚህ የኹጥባው ዋና ኃይማኖታዊ መሠረት ሙስሊሞች በሁሉም ዘመናት ለዘለዓለም መከተል ያለባቸው ቋሚ መንገድ ለመጠቆም ነበር፡፡

በዚሁ መልክ ደግሞ ሙናፊቆችና አፈንጋጮች ከአላህና መልዕክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) አፈንግጠው ህዝቡን ከዚህ የሐቅ መንገድ በማራቅ ለማሳሳት እንዳበቁ ተረጋግጧል፡፡

### *የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ንግግር አሰኳል*

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በአንክሮና በአጽንኦት ያነሱት ዋነኛው ርዕስ የአሥራ ሁለቱ ኢማሞች መሪነትና ለነዚህ ኢማሞች ቃል በመግባት ታማኝነትን ማሳየትና በዚህ ጉዳይ ፀንቶ መኖርን በተመለከተ ነበር፡፡

በአጠቃላዩ ኹጥባ (ንግግር) ውስጥ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በሶስት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ያጠነጠኑ ነበር፡-

1. የአሥራ ሁለቱን ኢማሞች መሪነትና ለነዚህ ኢማሞች ቃል በመግባት እስከ መጨረሻው በቃሉና በታማኝነት መቆየት ግዴታን አስመልክቶ ግልጽና ቀጥተኛ ነጥቦችን ማስቀመጥ፣
2. ለመሪነት የተመረጡ አካላትንና መሪነትን (ኢማምነትን) አስመልክቶ ያለውን ዋና ጉዳይና ዓላማ በመግቢያ መልኩ ማስተዋወቅና ግልጽ ማድረግ፣
3. የመሪነትን (ኢማምነትን) ጉዳዮችና የማህበራዊ ሚና ገደቦችንና ጥቅሞችን አስመልክቶ በቂ ገለጻ መስጠት፡፡

## *በኹጥባው ላይ የተነሱ ርዕሶች አኃዛዊ ትንተና*

ቀጥሎ የሚቀርበው በኹጥባው ላይ የተነሱ አበይት ርዕሶችና እነዚህ ርዕሶች (ጉዳዮች) የተነሱባቸውን ቦታዎች በአኃዝ (በቁጥር) ምን ያህል እንደነበሩ ለማስገንዘብ ነው፡፡

## *ሀ. የኹጥባው አበይት ርዕሶች*

ቀጥሎ ያለው ሠንጠረዥ የተነሱ አበይት ርዕሶች ስንት ጊዜ በተደጋጋሚ እንደተጠቀሱ (ስንት ቦታ እንደተነሱ) አኃዛዊ ማጠቃለያ ይሰጣል፡፡

| *ርዕሰ ጉዳዮች* | *ቦታዎች (ምን ያህል ጊዜ ተጠቀሱ)* |
|---|---|
| መለኮታዊ ባህሪያት | 150 ቦታዎች |
| ለዓሊ መሪነት ቃል መግባትና ታማኝ መሆን | 50 ቦታዎች |
| ለኢማሞች መሪነት ቃል መግባት | 10 ቦታዎች |
| የአሚረል ሙዕሚኒን ዓሊ ድንቅ ባህሪያትና ገድሎች | 20 ቦታዎች |
| ኢማም መህዲ | 20 ቦታዎች |
| የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ቤተሰቦች ወዳጆችና ጠላቶች | 25 ቦታዎች |
| ለኢማሞቹ ቃለ መሐላ መፈጸምና ድምጽ መስጠት | 10 ቦታዎች |
| ቁርአንና ትርጉሙ (ተፍሲር) | 12 ቦታዎች |
| ሐራምና ሐላል ጉዳዮች | 20 ቦታዎች |

## *ለ. በኹጥባው ወስጥ የተጠቀሱ የተባረኩ ስሞች*

| *ርዕሰ ጉዳዮች* | *ቦታዎች (ምን ያህል ጊዜ ተጠቀሱ)* |
|---|---|
| ‘ዓሊ’ የሚለው ስም | 40 ቦታዎች |
| ‘ኢማሞች’ (አኢማህ) | 10 ቦታዎች |
| ‘መህዲ’ የሚለው ስም | 4 ቦታዎች |

በኹጥባው ውስጥ የተነገሩ አብዛኛው አረፍተ ነገሮች በዓሊ ዙሪያ የሚያውጠነጥኑ ነበሩ፡፡ ስለዚህ በርካታ ተውላጠ ስሞች፣ ገላጭ ቃላትና የመሳሰሉት ቃላት ዓሊን የሚያመለክቱ ነበሩ፡፡

እነዚህ በአኃዝ የተቀመጡ ነገሮችን ማካተት የተፈለገበት ዋናው ምክንያት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እነዚህን ስሞች በተደጋጋሚ በበርካታ ቦታዎች ማንሳታቸው ለኹጥባው የተሰጠውን ከፍተኛ በታና የተነሱትን አበይት ጉዳዮች ግልጽ ያደርጋል በሚል እሳቤ ነው፡፡

## ሐ. በኹጥባው ውስጥ የተጠቀሱ የቁርአን አንቀጾች

ሀምሳ /50/ የቁርአን አንቀጾች በኹጥባው ውስጥ ተወስተዋል፡፡ ይህ የሚያመለክተው ይህ የገዲር ጉዳይ ከቁርአን ጋር ያለው ቁርኝትና ግንኙነት ምን ያህል የጠነከረ መሆኑን ነው፡፡

# 4

# በገዲር ኹጥባ ዙሪያ ያሉ ጥናቶችና ትንታኔዎች

በኢስላም ውስጥ በዋና ማጣቀሻነት (ዋቢ መጽሐፍትነት) የሚታወቁትን መጽሐፍት የጻፉ ታዋቂ ጸሐፍት የገዲር ኹጥባን ይዘትና አመዘጋገብ በተመለከተ ጥናቶች አድርገዋል፡፡ በሐዲሱ ዘገባና ትረካ ዙሪያ ያሉትን ሰዎች ማንነትና ስብዕና አስመልክቶ አጠቃላይ ምርመራ በማድረግ በትክክለኛነታቸው ላይ ወስነዋል፡፡ በተጨማሪም "ዊላያ" የሚለው ቃል የሚሰጠውን አውዳዊና ቀጥተኛ ትርጉም ላይ በቂ ገለጻ ሰጥተዋል፡፡ ይህ ደግሞ የኹጥባው ዋና መሠረት ነው፡፡

## የገዲር ኹጥባ ዋቢ መጽሐፍት (Bibliography)

የዚህ ኹጥበ ታሪክ አሥራ አራት ምዕተ ዓመታት ወደ ኋላ ይመለሳል፡፡ ከዙል ሂጃህ 18፣ 10ኛው ዓመተ ሂጅራ ጀምሮ ጸሐፊዎች ዘግበው ለማቆየት ጥረት አድርገዋል፡፡ መጽሐፍት የዚህ ኹጥባ ዋና ጠባቂ ሆነው አገልግለዋል፡፡ በአላህ ፈቃድ ይህንን ክስተት ለመዘገብና ለትውልድ ለማቆየት የተዘጋጁ ሰዎች በአጠቃላይ መጽሐፍትና በግል ማህደሮቻቸው በመዘገብ ለማቆየት ችለዋል፡፡

**አቡ ሳዲቅ ሱሌይም ቢን ቄይስ አል-ሒላሊ** - የቅዱሱ ነብይ (ሰ.ዐ.ወ) ታላቅ ሰሃባ የነበረና በ76 ሂጅራ የሞተ- ይህንን ኃላፊነት በመወሰድ ፊር ቀዳጅ የነበረ ሰው ነው፡፡ በመጽሐፉ ውስጥ በበርካታ ቦታዎች ላይ የገዲርን ክስተት

ጠቅሰዋል፡፡ የዕለተ ገዲርን ክስተቶች በሚመለከት አንድ ምዕራፍ ሙሉ በመስጠት ዝርዝር ጉዳዮችን ጽፏል፡፡ ይህንን መጽሐፍ የጻፈወ የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሐዲሶች እንዳይዘገቡ በጥብቅ የከለከለበት ዘመን ውስጥ ነበር፡፡ ጉዳዩ ለትውልድ ይቆይ ዘንድ የሱሌይምን መጽሐፍ ጠብቆ ያቆየው ኃያሉ አላህ ነው፡፡ መጽሐፉ ግን በሙስሊም ሀገሮች ውስጥ በስፋት ይገኛል፡፡ በተጨማሪም ታሪክ ወደ አል-ከሊል ቢን አህመድ አል-ፈራሂዲ መጽሐፍ ይመራናል፡፡ አል-ከሊል በ175 ዓመተ ሂጅራ የሞተ ታዋቂ የቋንቋ ሊቅ (ሊንግዊስት) ነበር፡፡ የገዲር ኹጥባ የተዘገበበት የመጀመሪያውን መጽሐፍ የጻፈ ታላቅ ሰው ነበር፡፡

ከዚያም በኋላ የገዲርን ክስተት በተመለከተ በርካታ መጽሐፍት ተገኝተዋል፡፡ ነገር ግን መጽሐፍቱ ይህን ርዕሰ ጉዳይ አስመልክቶ እንግዳ የሆኑ አረፍተ ነገሮችና ቃላት ያሉባቸው ነበሩ፡፡

አቡል መአሊ አል ጁዌይኒ (በ470 ዓመተ ሂጅራ የሞተ) እንዲህ ማለቱ ይነገራል፡- "በባግዳድ ውስጥ በአንድ የመጽሐፍ ሻጭ እጅ ላይ አንድ መጽሐፍ አየሁ፡፡ በመጽሐፍ የሽፋን ገጽ ላይ የሚከተለው ርዕስ ተጽፏል፡- "የዓሊን ለመሪነት መመረጥ አስመልክቶ ያሉ ሐዲሶች የትረካ መንገዶች፣ 28ኛ ቅጽ"፡፡ ከዚያም ሌላ ቅጽ ይከተል ነበር፡፡

ኢብን ኩሰይር ሲናገር፡- "የገዲር ኹምን ክስተት በተመለከተ ሙሐመድ ቢን ጀሪር አል-ጠበሪ በሁለት ሙሉ ጥራዞች ያጠናቀረውን ትረካዎች ለማየት ችዬ ነበር" ብሏል፡፡

የኢስላም ታዋቂ ምሁራን ይህንን ርዕሰ ጉዳይ አስመልክተው ራሳቸውን የቻሉ መጽሐፍት አጠናቅረዋል፡፡

ሰይድ አብዱል አዚዝ አል ጠባጠባኢ የገዲርን ኹጥባ በመጥቀስ የተከሰቱትን ድርጊቶች የሚተርኩ የ148 መጽሐፍት ርዕስ ዝርዝር ማሰባሰባቸው ይነገራል፡፡ ይህ መጽሐፍም፡- **"አል-ገዲር ፊ ቱራስ አል-ኢስላሚ"** ይባላል፡፡

በመጨረሻም ታላቁ መሪ መሐመድ አል-አንሳሪ "ገዲር ዳር አዬኔዬ ኪታብ" ማለትም 'ገዲር በመጽሐፍት እይታ' በሚል ርዕስ አንድ መጽሐፍ አጠናቅረዋል፡፡ በዚህ መጽሐፍ ውሰጥ ስለ ገዲር ኹጥባና በነዛ ዕለታት ስለነበሩ ሥነ ሥርዓቶች የሚያወሱ የ414 መጽሐፍት ርዕሶች ዝርዝር ጠቅሰዋል፡፡ የእያንዳንዱን መጽሐፍ ማጠቃሻዎችም
(ዋቢ መጽሐፍትም) አካተዋል፡፡

የሐሚድ ሁሴይን አል ሂንዲ "አበቃቱል አንዋር"፣ የአብዱል ሁሴይን አል አሚኒ አል ነጃፊ "አል ገዲር" እና የዓሊ አል ሁሴይኒ አል ሚላኒ 'ነፈሀቱል አዝሐር' የተሰኙ መጽሐፍት ስለ ገዲር ሐዲስና የሐዲሱ ተራኪዎች ጥናት አስመልክቶ ከሚገኙት በርካታ መጽሐፍት ውስጥ ተቀዳሚውን ደረጃ የያዙና ምርጥ የሆኑ ናቸው፡፡

በነዚህ መጽሐፍት ውሰጥ የዘጋቢዎቹና ተራኪዎቹ አሃዛዊ ትንትኔ ተሰጥቷል፡፡ የተራኪዎቹንና የዘጋቢዎቹን ትክክለኛነትና ስብዕናን በተመለከተም ዝርዝር ጥናት ተደርጓል፡፡ የአዘጋገቡ ታሪክና የክስተቱ አተራረክ ዘይቤም በዝርዝረ ተቀምጧል፡፡ እነዚህ መጽሐፍት የገዲርን ክስተት ያህል ከፍተኛ የዘጋቢና የተራኪ ቁጥር ያለው ጉዳይ አለመኖሩን ያረጋግጣሉ፡፡ ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰሃባ የሆኑ ከ 120 በላይ የሚሆኑ ግለሰቦች የገዲርን ክስተት ተርከዋል፡፡ ከሰሃቦች

በኋላ ያሉት ትውልዶች (ታቢኢን) እንዲሁም ቀጥሎ ያሉት ትውልዶች የክስተቱን ታሪክ አስተላልፈዋል፡፡

የጣሚዎች ሚናም ሰይጠቀስ የሚታለፍ ነገር አይደለም፡፡ በተለያዩ አጋጣሚዎችና ሥነ ሥርዓቶች ላይ ገጣሚዎች በርካታ ግጥሞችን በመጻፍና በማነብነብ ክስተቱ በየጊዜው እንዲንሰራራና ህያው ሆኖ ለትውልድ እንዲቆይ ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል፡፡ በወቅቱ የነበረውን እያንዳንዱን ድርጊት በግልጽ አስቀምጠዋል፡፡ እነዚህ ግጥሞች "አል-ገዲር" በተሰኘው ባለ አሥራ አንድ ጥራዝ (ቮሊዩም) የአል አሚኒ መጽሐፍ ውሰጥ ተጠናቅረዋል፡፡

## የኹጥባው ዋቢ መጽሐፍትና የዘገባ ሂደት

ሙሉውን የገዲር ኹጥባ ያካተቱ የታተሙ ታዋቂ መጽሐፍት በቁጥር ሰባት ብቻ ናቸው፡፡ ለወደፊቱ በሚጠቀሱት በነዚህ ዋቢ መጽሐፍት ውስጥ የሚገኘው ትረካ የተገኘው ደግሞ ከተከታታይ ትረካዎች (አሳኒድ ሙተሲለህ) ሲሆን በሶስት አቅጣጫዎች ሪዋያ (ትረካ) ተዘግቧል፡-

1. **የኢማም ሙሐመድ አል-ባቂር ሪዋህ፡-** ይህ ሪዋያ በ "ረውደቱል ዋኢዚን"፣ ክፍል **1**፣ ገጽ **89**፤ በ"አል-ኢህቲጃጅ" ክፍል **1**፣ ገጽ **66**፣ እና በ"አል የቂን"፣ ገጽ **343** ተጠናቅሮ ይገኛል፡፡

2. **የዘይድ ቢን አርቀም *ሪዋያ***፡- ይህ ሪዋያ በ ***አል-ዑደዱል ቀዊያህ*** ገጽ 169፣ ***አል-ተህሲን*** ገጽ 587 እና **አል-ሲራጠል ሙስተቂም**፣ ክፍል አንድ፣ ገጽ 301- ተከታታይነት ባለው መልኩ ተዘግቧል፡፡

3. **የሁዘይፋህ ቢን የማን ሪዋያ፡-** ይህ ሪዋያ ተከታታይነት ባለው መልኩ በ ***አል-ኢቅባል*** ገጽ 454፣456፣ተጠቅሷል፡፡

ቀጥሎ የነዚህ ሦስቱ መንገዶች (ሪዋያዎች) ዝርዝር ሰንሰለተ-ሐዲስ ይቀርባል፡፡

## የኢማም ሙሐመድ አል-ባቂር ሪዋያ በሁለት ሰነዶች፡-

1. አህመድ ቢን ዓሊ ቢን አቢ መንሱር አል-ጢብሪሲ፣ አቡ-ጀዕፈር መህዲ ቢን አቢል ሐሪስ አል ሁሴይኒ አል-መራሺ፣ አቡ ዓሊ አል-ሐሰን ቢን አቡ ጃልፈር መሐመድ ቢን ሐሰን አል-ጡሲ፣ አቡ ጃዕፈር፣ የሆኑ ጀመዓዎች፣ አቡ ሙሐመድ ሓሩን ቢን ሙሳ አል-ተልዓከብሪ፣ አቡ ዓሊ ሙህመድ ቢን ሐማም፣ ዓሊ አል-ሱሪ፣አቡ ሙህመድ አል-አላዊ (የአል አፍጠስ ተወላጅና ከደጋጎቹ የአላህ ባሪያዎች የነበረ)፣ ሴይፍ ቢን ኡሜሪያና ሳሊህ ቢን አቀባህ፣ ቁይስ ቢን ሰምዓን፣ አልቀማ ቢን መህመድ አል-ሐድራሚ፣ አቡ ጃዕፈር ሙሐመድ አል-ባቂር . . .
2. ሰይድ ኢብን ጣውስ፣ አህመድ ቢን ሙህመድ አል-ጠበሪ አለ ከሊሊ፣ ሙህመድ ቢን አቢ በክር ቢን አብድረህማን፣ አል ሀሰን ቢን ዓሊ አቡ ሙህመድ አል-ዴይኑሪ፣ ሙሐመድ ቢን ሙሳ አል-ሐመዳኒ፣ ሙሐመድ ቢን ኻሊድ አል-ጠያልሲ፣ ሴይፍ ቢን ኡሜሪያ፣ አቀባ ቁይስ ቢን ሰምዓን፣ አልቀማ ቢን ሙሐመድ አል-ሐድራሚ፣ አቡ ጃዕፈር ሙሐመድ አልብቂር--

**የዘይድ ቢን አርቀም ሪዋያ በአንድ ሰነድ፡-**

3. ሰይድ ኢብን ጣውስ፣ አል-ሐሰን ቢን አህመድ አል-ጃዋኒ፣ ሙሐመድ ቢን አብደላህ አል- ሸይባኒ፣ መሐመድ ቢን ጀሪር አል-ጠበሪ እና ሓሩን ቢን ዒሳ አል-በለዲ፣ሐሚድ ቢን ረቢዕ አል-ኸዛዝ፣ የዚድ ቢን ሓሩን፣ ኑህ ቢን ሙበሽር፣ ወሊድ ቢን ሷሊህ ቢን ኢምረአት (ባለቤት/ሚስት) ዘይድ ቢን አርቀም እና ዘይድ ቢን አርቀም. . .

**የሁዘይፋ ቢን አል-የማን ሪዋያህ በአንድ ሰነድ፡-**

4. ሰይድ ኢብን ጣውስ፣ ***አል-ነሸር ወ ጠይ*** የተሰኘው መጽሀፍ ደራሲ፣አህመድ ቢን ሙሐለብ፣ ሸሪፍ አቡልቃሲም ዓሊ ቢን ሙሀመድ ቢ ዓሊ ቢን አል-ቃሲም አል-ሸዕራኒ፣ ከአባቱ፣ ሰለማህ ቢን አል-ፊድል አል አንሳሪ፣ አቡ መርየም፣ ቂይስ ቢን ሐያን (ወይም ሐናን)፣አጢያ አል- ሰዕዲ፣ ሁዘይፋ ቢን የማን . . .

ይህ የገዲር ኹጥባ ዘገባና የትረካዎቹ ሰንሰለት (አሳኒድ) ዝርዝር መግለጫ ነው፡፡ የኹጥባው አንቀጾች በትክክለኛው የዘገባ ሥርዓት በተለያዩ ዋቢ መጽሀፍት ውስጥ ተዘግበው ይገኛሉ፡፡ እነዚህ መጽሀፍት ***አበቃቱል አንዋር*** በተሰኘው በሰይድ ሓሚድ ሁሴይን አል-ሂንዲ የተጠናቀረው ባለ አስር ጥራዝ መጽሀፍና በአላማህ አል-አማኒ የተጻፈው ***ገዲር*** የተሰኘ መጽሀፍ ውስጥ በዝርዝር ተዘግበዋል፡፡

## የኹጥባው ጽሁፍ ግምገማ

***ኢህቲጃጅ*** በተሰኘው *መጽሀፍ* ውስጥ የተዘገበውን የገዲር ሙሉ ኹጥባ *መሠረት* በማድረግ የኹጥባው ጽሁፍ ለብቻው ብዙ ጊዜ በተለያዩ *መዝገቦች* *ታትሟል*፡፡ ቀጥሎ የቀረበው የገዲር ኹጥባ፣ የኢማም አል-ባቂር፣ የሁዘይፋ ቢን የማንና የዘይድ ቢን አርቀም *ሪዋያዎችን* መሰረት በማድረግ በሰባት ዋቢ *መጽሀፍት* ውስጥ ተገምግሞና አርትኦት ተደርጎበት የቀረበ ነው፡፡ እነዚህ *መጽሀፍትም*፡- *ረውደቱል ዋኢዚን፣ አል-ኢህቲጃጅ፣ አል-ዑደዱል ቀዊያህ፣ አልየቂን፣ አል- ተህሲን፣ አል-ኢቅባል* እና *አል-ሲራጠል ሙስተቂም* ናቸው፡፡

የበለጠ ትክክለኛ የሆነውን ጽሁፍ ለመለየት በመጽሀፍቱ ውስጥ የተዘገቡትን የኹጥባው ጽሁፎችን የማወዳደርና የማነጻጸር ሥራ ተሠርቷል፡፡

ከዚህ በታች የቀረበው በአስራ አንድ ርዕሰ ጉዳዮች የተከፈለ ሙሉ የገዲር ኹጥባና ወደ አማርኛ ለመተርጎም የተደረገ ሙከራ ሲሆን ትክክለኛውን መልዕክት በሚገባ ለመረዳት አረብኛውን ማንበብና ማጥናት አማራጭ የሌለው እርምጃ ነው፡፡ ለዚህም ይመች ዘንድ ሙሉው የአረቢኛ ኹጥባ ከአማርኛ የሙከራ ትርጉም ቀጥሎ በዚህ መጽሀፍ ዉስጥ ተካቷል፡፡

# 5

# የገዲር ኹጥባ

## በርካታ ቁጥር ያላቸው ሙስሊሞች በተሰበሰቡበት፣ ለሰው ልጆች በሙሉ በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የተደረገ የመጨረሻው ህዝባዊ ንግግር (ኹጥባ)

***እጅግ ርህሩህና መሃሪ በሆነው በአላህ ስም***

### ክፍል አንድ
### አላህን ማመስገንና ማወደስ

*ምሥጋና ለአላህ ነው፤ በአንድነቱ የላቀ፣ በብቸኝነቱ (ለፍጡራኑ) ቅርብ የሆነ፣ በስልጣኑና በችሎታው የመጠቀ፣ ረድዔቱ ወደር የሌለው(የስሞቹ ማዕዘናት የከበሩ)፣ ነገሮች ሁሉ ባሉበት ዕውቀቱ ሁሉን ነገር ያከበበ (በመጠቀና በላቀ ደረጃ ሆኖ ዕውቀቱ ሁሉን ነገር ያካበበ)፣ በኃይሉ (በችሎታው)ና በማስረጃው*

መላውን ፍጡራን በቁጥጥር ሥር ያደረገ፣ ሁሌም ምሥጋና የተገባውና ምንጊዜም የሚመሰገን፣ ለክብሩ ወሰን የሌለው፣ ፍጥረታትን የሚያስገኝና ዳግምም የሚፈጥር፣ ሁሉም ነገር ወደሱ ተመላሽ ነው፣ ከፍ ያሉትን (ሰማያትን) የሠራና የተዘረጉትን (ፕላኔቶችን-መሬትን) የሚያሰፋ፣ በፕላኔቶችና በሰማያት ላይ የበላይ የሆነ፣ ቅዱስና ከማይገባው ነገር ሁሉ የጠራ፣የመላዕክትና የመንፈሱ ጌታ፡፡

ለፍጡራኑ ሁሉ የሚለግስ፣ ላስገኛቸው ፍጡራን ሁሉ ፀጋውን የሚያራዝም (ባስገኛቸው ፍጡራን በሙሉ ላይ የበላይ የሆነ)፣እሱ ሁሉንም ዓይኖች ያያል፣ ዓይኖች ግን አያዩትም፡፡ ለጋስ፣ቻይና ትዕግስተኛ የሆነ፣ ምህረቱ ከሁሉም ነገር በላይ የሰፋ፣በፀጋው በጎ ዋለላቸው፣ ለብቀላ የማይቸኩል፣ቅጣት ለሚገባቸው እንኳ ለቅጣታቸው ተነሳሽነት የማያሳይ፡፡

ምስጢሮችን ሁሉ ያውቃል፣ልቦች የሚደብቁትን ሁሉ ዐዋቂ ነው፣ ድብቅ ነገሮች ከሱ አይሰወሩም፣ ስውር ነገሮችም ለጥርጣሬ አይዳርጉትም፡፡ ሁሉን ነገር (በዕውቀቱ) ያካብባል፣ በሁሉም ነገር ላይ አሸናፊም ነው፡፡ በሁሉም ነገር ላይ ብርቱ ነው፣ በሁሉም ነገር ላይ ችሎታ አለው፡፡ የሱ አምሳያ አንዳችም ነገር የለም፣ እሱ ‹አንድን ነገር› ምንም ነገር ባልነበረ ጊዜ ያስገኘ ነው፡፡ ዘለዓለማዊና በፍትህ የሚፈርድ ጌታ ነው፣ ከሱ በቀር አምላክ ለም፣ ኃያልና ጥበበኛ ነው፡፡

በእይታዎች ከመታየት የላቀ ሲሆን እሱ ሁሉንም እይታዎች ይይዛል፡፡ እሱ ቅን ፈራጅ፣ርህሩህና ሁሉን ነገር ውስጠ አዋቂ ነው፡፡ ማንም ሰው አይቶ ሊገልጸውና

ስለእሱ መናገር አይችልም (ማንም ሰው በእይታም ሆነ በአዕምሮ ገለጻው ላይ ሊደርስ አይቻለውም)፣ኃያሉና አሸናፊው ስለእራሱ ካመላከታቸው በስተቀር ማንም ሰው እንዴት እንደሆነ በሚስጥርም ሆነ በገሀድ ሊያውቅ አይችልም፡፡

እሱ ቅድስናው ዘመናትን በሙሉ የሞላ አላህ መሆኑን እመሰክራለሁ፣ ብርሃኑ ለዘለዓለም የሚያብረቀርቅ፣ አንድንም አማካሪ ሳያማክር ትዕዛዛቱን የሚያስፈጽም፣ በዕቅዱ ውስጥ ተጋሪ የሌለውና በአስተዳደሩና በማስተናበሩ ውስጥ እንከንና ልዩነት የሌለው፡፡

ያስገኛቸውን ነገሮች ያለምንም ምሳሌ/ናሙና የቀረጸና የፈጠራቸውን ፍጡራን ያለ ምንም እርዳታ፣ያለ ግዴታና ኃላፊነት እንዲሁም የሆነ መፍትሔ የማግኘት ፍላጎት ሳይኖረው የፈጠራቸው፣ (በፈቃዱ) አስገኛት፣ ሆነችም፡፡(በፈቃዱ) ቀረጻት፣ ሆናም ተገኘች፡፡ እነሆ ከሱ በቀር አምላክ የሌለ እሱ አላህ ነው፡፡ በጥበቡ የመጠቀና የተግባሩ መልካምነት እጅግ ያማረ፣ፍጹም የማይጨቁን ፍትሓዊና ሁሉም ነገር ወደሱ የሚመለስ የሆነ እጅግ ሊጋስ ጌታ፡፡

አላህ፣ እሱ በክብሩ ፊት ሁሉ ነገር የተዋረደና በኃይሉ ፊት ሁሉም ነገር የወደቀ ጌታ መሆኑን እመሰክራለሁ፡፡ በችሎታው ፊት ሁሉም ነገር እጅ የሰጠና በግርማ ምገሱ ፊት ሁሉም ነገር ዝቅ ያለ፣የሁሉም ግዛቶች ንጉስና ሰማያዊ አካላትን በየምህዋራቸው የሚያንቀሳቅሳቸውና የሚያሽከረክራቸው፣ እስከ ተወሰነላቸው ጊዜ ድረስ እያንዳንዳቸው መንገዳቸውን ጠብቀው የሚጓዙትን ፀሓይና ጨረቃን ያገራ፣ቀንን በሌሊት ይተካል፣ሌሊትንም በቀን ይተካል፣አንዱ ሌላውን በፍጥነት ፈላጊ (ሁለቱንም ለመቀያየር የሚያጣድፍ ሲሆን)፡፡

እያንዳንዱን አምባገነን ጨቋኝ የሚያወድምና እያንዳንዱን አፈንጋጭ ሰይጣን የሚያጠፉ፡፡

ተቃዋሚ ኃይልም ሆነ ወዳጅ(አጋር) ኖሮት አያውቅም፡፡ ብቸኛ፣ የተብቃቃ፣ የማይወልድ፣ የማይወለድና አንዳችም አምሳያ የሌለው፣ ብቸኛው አምላክ፣ ክቡር ጌታ፡፡

በመሻቱ የሚፈጽም፣ በፈቃዱ የሚከውን፣ በእውቀቱ ሁሉ ነገር የሚሆን (ይሻል፣ ይፈጸማልም፤ ይፈቅዳል፣ ይከናወናልም፤ ያውቃል፣ ይሆናልም፡፡) ሞትን ያስከትላል፣ ህይወትም ይሰጣል፣ ያደኀያል፣ ሀብት ያጎናጥፋልም፤ (ሰዎች) እንዲስቁ ያደርጋል፣ እንዲያለቅሱም ያደርጋል፤ ያቀርባል፣ ያርቃልም፣ ይነሳል፣ ይሰጣልም፤ ክብርና ሚሰጋና ለርሱ ነው፣ መልካም ነገሮች ሁሉ በእጁ ናቸው፣ ሁሉንም ነገር ማድረግ የሚችል ነው፡፡

ሌሊትን ቀን ውስጥ ያስገባል፣ ቀንንም ሌሊት ውስጥ ያስገባል፤ ከሱ በቀር አምላክ የለም፤እሱ ኃያልና መሐሪ ነውን፡፡ ተማጽኖን የሚሰማ፣ለፀጋው የማይሰስት (ስጦታው የበረከተ)፣ እስትንፋሶችን የሚቆጥር፣ የሰዎችና የጋኔን (ጂን) ጌታ፡፡ አንዳችም የሚቸግረው ነገር የለም፣ የችግርተኞች የልመና ለቅሶ አይጫነውም፣ የችክ ባዮች ችክታም (ሳያቋርጡ በተደጋጋሚ ችክ ብለው የሚጠይቁ/የሚለምኑ የሰዎች ልመና) አያስቆጣውም፡፡ ጻድቃንን የሚጠብቅ፣ ለብልጹጋን ስኬትን ያጎናጸፈ፣ እሱ የአማኞች ጠባቂና መሪ ነው፣ የዓለማት ጌታ ነው፡፡ በማንኛውም ሁኔታ በእያንዳንዱ ፍጥረት ሊመሰግንና ሊወደስ የሚገባ ጌታ፡፡

(ስለዚህ) አመሰግናዋለሁ፣ አወድሰዋለሁ፡፡ በደስታም ሆነ በሐዘን፣ በምቾትም ሆነ በጥበት፣ በጭንቅ ጊዜም ሆነ በእረፍት ወቅት አመግነዋለሁ፡፡ በሱ (በአላህ)፣ በመላዕክቱ (በመላኢካዎቹ)፣ በመጽሀፍቱ (በኪታቦች)ና በመልዕክተኞች አምናለሁ፡፡

ትዕዛዛቱን እሰማለሁ፣ እታዘዛለሁም፣ እሱን ወደሚያስደስቱ ማንኛውም ነገሮች እሽቀዳደማለሁ፣ ለፍርዱ እጅ እሰጣለሁ፣ እሱን ለመታዘዝ በመከጀል፣ ቅጣቱን በመፍራት፡፡ እሱ አላህ ከሴራው ነጻ መሆን የማያስተማምን፣ ቅጣቱ መቼ እንደሚደርስ የማይገመት (በኢ-ፍትሃዊነት ተግባር የማይጠረጠርና የማይፈራ) ጌታ ነውና፡፡

## ክፍል ሁለት
## ከአላህ የመጣን እጅግ ጥብቅ ትዕዛዝ የማስተላለፍ ዝግጅት

በአምልኮ ለርሱ ማደሬንና አገልጋይነቴን በራሴ ላይ አረጋግጣለሁ፣ እሱ ደግሞ ጌትነት እንደሚገባው እመሰክራለሁ፡፡ ወደኔ የመጣውን መልዕክት (እኔ ላይ የወረደውን) ከማድረስ ወደ ኃላ አልልም፡፡ ይህን ካላደርግኩ ማንም ሊመልሰውና ሊከላከልልኝ የማይችል አደጋ (ቅጣት) ይወርድብኛል ብዬ እሰጋለሁና፤ የተሰጠኝን መልዕክት ካላስተላለፍኩ የፈለገ የረቀቀ ዘዴ ያለው ሰውም ሆነ የቅርብ ወዳጅ ሊመልሰው የማይችል ቅጣት በኔ ላይ ተገቢ ይሆናል ብዬ እፈራለሁና፡፡ ከሱ በቀር አምላክ የለም፡፡

እነሆ ዓሊን አስመልክቶ በኔ ላይ የወረደውን (መልዕክት) ካላስተላለፍኩኝ መልዕክቱን በሙሉ በጭራሽ እንዳላስተላለፍኩ እንደሆነ አስጠንቅቆኛል፡፡ በእርግጥ የተቀደሰና የበላይ የሆነው ጌታ (ከሰዎች ትንኮሳ) የደህንነት ዋስትና ሰጥቶኛል፣ እሱ አላህ (ዋስትናው) በቂ የሆነና ፀጋውና ልግስናው የላቀ ነውና፡፡

እነሆ ወህይ (ራዕይ) ወደኔ መጣ፡- **እጅግ ርህሩህና መሓሪ በሆነው በአላህ ስም፣አንተ መልዕክተኛ ሆይ! ከጌታህ ወደ አንተ የተወረደውን (ዓሊን አስመልክቶ፣ ማለትም የዓሊ ቢን አቢ ጧሊብን ኺላፋህ (ተተኪነትና መሪነት በማስመልከት) መልዕክት አድርስ (ተናገር)! ይህንን ካላደረግክ የአላህን መልዕክት ጭራሽ አድርሰህ እንደማታውቅ ነው፡፡ አላህ ከሰዎች ሸር (እኩይ ተግባር) የደህንነት ዋስትና ይሰጠሀል (ይጠብቀሀል)፡፡**

ሰዎች ሆይ! የበላይ የሆነው አላህ እኔ ላይ ያወረደውን ከማስተላለፍ ወደ ኃላ ብዬ አላውቅም፡፡ ይህ የቁርአን አንቀጽ የወረደበትን ምክንያት ልገልጹላችሁና ላስረዳችሁ እወዳለሁ፡፡ መልአኩ ጂብሪል (ገብርኤል) የጌታዬን ትዕዛዝ ይዞ ሦስት ጊዜ ወደኔ መጣ፡፡ እነሆ የአማኞች ጠባቂ የሆነው ጌታ በዚህ ቦታ ሆኜ ዓሊይ ቢን አቢ ጧሊብ ወንድሜ፣ጉዳይ አስፈፃሚዬ /ወራሼ (ወሲዪ)፣ በህዝቤ ላይ ተተኪ (ኸሊፈቲ)ና ከኔ በኃላ መሪ (ኢማም ሚን በዕዲ) መሆኑን ለእያንዳንዱ ነጭም ሆነ ጥቁር አሳውቃለሁ፡፡ እነሆ ዓሊ ከኔ አኳያ ያለው ቦታ ሓሩን ለሙሳ ካለው ቦታ ጋር አንድ ነው፡፡ ልዩነቱ ከኔ በኃላ ነቢይ አለመኖሩ ብቻ ነው፡፡ እሱ (ዓሊ) ከአላህና መልዕክተኛው በኃላ ወሊያችሁ (መሪያችሁ) ነው፡፡ እነሆ ይህን ጉዳይ አስመለከቶ አላህ ከመጽሀፉ አያህ (አንቀጽ) አወረደ፡-

***ወሊያችሁ (መሪያችሁና አዛዣችሁ) አላህና መልዕክተኛው፣ እነዚያም ያመኑት ብቻ ናቸው፤ (እነርሱ) እነዚያ ሰላትን በደንቡ የሚሰግዱ፣ እነርሱም ያጎነበሱ ሆነው ምጽዋትን የሚሰጡ ናቸው፡፡ (5፡55)***

*ሰላትን ቀጥ አድርጎ ያቆመ፣ በሩኩዕ (በሰላት ጊዜ አጎንብሶ በሁለት መዳፎች ጉልበትን በመያዝ የሚፈጸም የሰላት ክፍል) ውስጥ ዘካትን (ምጽዋት) የሰጠና በማንኛውም ሁኔታ የአላህን ውዴታ የሚሻ ዓሊ ቢን አቢ ጧሊብ ነው፡፡*

ሰዎች ሆይ! አላህን የሚፈሩ ሰዎች ቁጥራቸውን መመናመኑን፣ ሙናፍቆች መበርከታቸውን፣ የወንጀለኞች አሻጥርና ሙስና መንሰራፋቱንና በኢስላም የሚቀልዱና የሚያሾፉ አታላዮች መብዛታቸውንና አላህ በቁርአኑ የገለጻቸው . . . ***በልቦቻቸው ውስጥ የሌለውን ነገር በምላሶቻቸው ይናገራሉ (48፡11)*** የተባለላቸው ሰዎች መኖራቸውን ስለማውቅ ይህንን መልዕክት የማስተላለፍ ሃላፊነት እንዲነሳልኝና ይቅርታ እንዲደረግልኝ ጂብራል አላህን እንዲማፀንልኝ ጠይቄ ነበር፡፡ ከዚህም አልፎ ብዙ ጊዜ በተለያዩ አጋጣሚዎች ያስቆጡኝና ያበሳጩኝ ሰዎች በመኖራቸውና እንዲያውም ***ጆሮ*** ብለው ስም እስከማውጣት የደረሱ ሰዎች መገኘታቸውን በማወቁ፣ እንዲህም ያሉት ዓሊ እኔ ባለሁበት ቦታ ሁሉ ከጎኔ ባለመታጣቱና ለሱ የሰጠሁትን ትኩረቴን በማየት ይህን ስም መስጠታቸውን ስለማውቅ፣ አላህም ይህንን አስመልክቶ (የቁርአን አያህ) አወረደ፡- ***እነሱም (ከመናፍቃን) እነዚያ ነቢዩን የሚያሰቃዩ እርሱም ጆሮ ነው (ወሬ ሰሚ ነው) የሚሉ አልሉ በላቸው፡፡ (9፡61)***

እንዲህ ያሉትን ሰዎች በስማቸው መጥራት ብፈለግ ልጠራቸው እችል ነበር፣ወይም ወደነሱ ማመልከት ብፈልግ ባመለከትኩ ነበር፡፡ በምልክታቸው መጋለጥ ብፈልግም ማድረግ እችል ነበር፡፡ ነገር ግን በአላህ እምልላሁ ጉዳያቸውን በክብር ያዝኩት፡፡

ይህ ሁሉ በእንዲህ እንዳለ ግን ዓሊን በተመለከተ የመጣውን ትዕዛዝ እስካላስተላፍኩ ድረስ አላህ በኔ አይደሰትም፡፡

ከዚያም ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የሚከተለውን ቀሩ፡- ***አንተ መልዕክተኛ ሆይ! ከጌታህ ወዳንተ የተወረደውን አድርስ፤ ባትሰራም መልዕክቱን አላደረስከም፤ አላህም ከሰዎች ይጠብቅሃል፤ አላህ ከሓዲዎችን ሕዝቦች አያቀናምና፡፡*** **(5፡67)**

## ክፍል ሦስት
## የዓሊ ቢን አቢ ጣሊብንና ቀጥሎ የሚመጡትን የአስራ ሁለት ኢማሞች መሪነትና ኢማምነትን በግልጽ ማወጅ

ሰዎች ሆይ! ይህንን የዓሊ ደረጃና ቦታ ሊትረዱና ሊትገነዘቡ ይገባል፡፡ አላህ ዓሊን መሪያችሁና ኢማማችሁ አድርጎ እንደመረጠውና እንደሾመው ማወቅና መቀበል ይገባችኃል፡፡ እሱን መታዘዝና መከተል በሙሐጂሮች ላይ፣ በአንሷሮችና በወዳጆቻቸው ላይ፣በከተማ ነዋሪዎችም ሆነ በበረሃ ነዋሪዎች (ዘላኖች) ላይ፣አረብና አረብ ባልሆነው ላይ በሙሉ ግዴታ ተደርጎ ተደንግጓል፡፡ ውሳኔውን መተግበር፣ቃላቱን መታዘዝና ትዕዛዛቱን መፈጸም በሁሉም ላይ ግዴታ ነው፡፡ እሱን የሚቃወሙና የሚቃረኑ የተረገሙ ናቸው፣ለሱ የሚታዘዙና

ዕውቅና የሚሰጡ የተባረኩ ናቸው፡፡ አላህ የተከታዮቹን፣የደጋፊዎቹንና የታዛዦቹን ኃጢአት ይምራቸዋል፡፡

ሰዎች ሆይ! ይህ ከእናንተ ጋር የምኖረኝ የመጨረሻው ስብሰባ ነው፡፡ በእንዲህ ዓይነት ስብስብ ፊት የምቆመው ለመጨረሻ ጊዜ መሆኑን እነግራችኃለሁ፡፡ ስለዚህ አድምጡኝ፣ ታዘዙ፣ ለአላህ ፍርድ እጅ ስጡ፡፡ ኃያሉና አሸናፊው አላህ አለቃችሁ (መውላችሁ) ነው፡፡ ከአላህ በኋላ ደግሞ አሁን ከፊታችሁ ቁሞ ንግግር (ኹጥባ) የሚያደርግላችሁ መልዕክተኛው ሙሐመድ አለቃችሁ (ወሊያችሁ) ነው፡፡ ከኔ በኃላ ደግሞ በጌታችሁ በአላህ ትዕዛዝ መሠረት ዓሊ አለቃችሁ (ወሊያችሁ)ና መሪያችሁ(ኢማማችሁ) ነው፡፡ በመቀጠል ደግሞ የኢማምነት (የመሪነት) ቦታው ከዓሊ አብራክ የሆኑት ለዙርያዬ (ለቤተዘሮቼ) ይሆናል፡፡ አላህና መልዕክተኛው ጋር (በትንሳዔ ቀን) እስክትገናኙ ድረስ የማሪነቱ (ኢማሚነቱ) ሹመት ለነሱ የፀና ነው፡፡

አላህ፣ መልዕክተኛውና እነሱ (ኢማሞቹ) ሀላል (ህጋዊ) ካደረጉት ነገር በስተቀር ሀላል የለም፤አላህ፣ ነቢዩና እነሱ ሀራም (ህገ-ወጥ/የተከለከለ) ካደረጉት ነገር ሌላ ሀራም የለም፡፡ አላህ ከመጽሀፉ ያስተማረኝን ዕውቀት፣ ስለ ሐላልና ሐራም ያሳወቀኝን ጥበብ ለሱ(ለዓሊ) አሳውቄያለሁ፡፡ ሁሉን ነገር ግልፅ አድርጌለታለሁ፡፡

ሰዎች ሆይ! አላህ በልቤ ውስጥ ያላስቀመጠው ዕውቀትና ጥበብ የለም፡፡ እኔ ደግሞ የተሰጠኝን ዕውቀትና ጥበብ የጻድቃን ቁንጮ (መሪ) ለሆነው (ለዓሊ) አስተላልፌያለሁ፡፡

አላህ በሱራህ አል-ያሲን ውስጥ የዘከረውን ግልጽ ኢማም (ኢማሙል ሙቢን) ዓሊን ያላስተማርኩት ዕውቀት የለም፡፡ . . . ***ነገሩን ሁሉ ግልጽ በሆነ መሪ ውስጥ አደረግነው፡፡ (36፡12)***

ሰዎች ሆይ! ከሱ አታፈንግጡ፣ ከሱ አትሽሹ፣ መሪነቱንና ስልጣኑም መቀበል አሻፈረን አትበሉ፡፡ ወደ ሐቅ (እውነት) የሚመራና በሐቅ የሚሰራ እሱ ነው፡፡ ሐሰትን የሚያወድምና ከእኩይ ተግባራት የሚከለክል እሱ ነው፡፡ በአላህ መንገድ ላይ ለሚደርስበት ትችት ይሉኝታ በፍጹም አያጠቃውም፡፡ እሱ በአላህና በመልዕክተኛው ያመነ የመጀመሪያው ሰው ነው፡፡ ከአላህ መልዕክተኛ ጋር ሆኖ አላህን የሚገዛ ማንም ወንድ ባልነበረበት ወቅት ከአላህ መልእክተኛ ጋር የነበረ ብቸኛው ሰው ነው፡፡ በኔ በማመን የቀደመው አንድም ሰው አልነበረም፡፡

ነፍሱን ለአላህ መልዕክተኛ ቤዛ ያደረገ ጀግና ነው፡፡ በአላህ ትዕዛዝ መሠረት በኔ ቦታ ሆኖ በመኝታ ቦታዬ ላይ እንዲተኛ አዘዝኩት፡፡ እሱም ነፍሱን ለኔ ፍዳእ (መስዋዕት) አድርጎ ትዕዛዙን ፈጸመ፡፡

ሰዎች ሆይ! አላህ(በሌሎች ላይ) ስለመረጠውና ብልጫ ስለሰጠው እናንተም ለሱ ብልጫ ስጡ፡፡ በእርግጥም አላህ ስለመረጠውና ስለሾመው ተቀበሉት፣ ወደሱም ዙሩ፡፡

ሰዎች ሆይ! እሱ በአላህ የተሾመ ኢማም (መሪ) ነው፡፡ ዊላያውን (መሪነቱን) የሚክድን ሰው አላህ ተውባውን (ንስሃውን) አይቀበልም፣ አይምርምም፡፡ ይህ

እሱን አስመልክቶ አላህ የወሰነውን ትዕዛዝ በሚክዱ ሰዎች ላይ የተሰጠ የማይቀለበስ ፍርድ ነው፡፡

(እንዲህ የሚያደርጉትን ሰዎች) እጅግ አሳማሚ የሆነን ቅጣት ለዘለዓለም ሊቀጣቸው ፈርዷል፡፡ ስለዚህ እሱን ከመቃወም ተጠንቀቁ፣ ማቀጣጠያዋ ሰውና ድንጋይ የሆነችዋን ለከሃዲዎች (ለካፊሮች) የተዘጋጀችዋን እሳት እንዳትገቡ ተጠንቀቁ፡፡

ሰዎች ሆይ! በአላህ እምላለሁ! ቀደምት ነቢያትና መልዕክተኞች ስለኔ ብስራት ተሰጥቷቸዋል፡፡ እኔ የነቢያትና የመልዕክተኞች መደምደሚያ ነኝ፣በሰማያትና በመሬቶች ነዋሪ ላይ (የአላህ) ሁጃህ (ማስረጃ) ነኝ፡፡ በዚህ ጥርጣሬ የገባው ሰው ካፊር (ከሃዲ) ነው፣ የመጀመሪያው የጀሂሊያ (ድንቁርና) ዘመን ኩፍር (ክህደት) ያለበት ሰው ነው፡፡ (በዛሬው ዕለት) የተናገርኩትንም የሚጠራጠር ሰው በእርግጥ በኔ ላይ በወረደው በሙሉ የሚጠራጠር ነው፡፡ ከኢማሞቹ (መሪዎቹ) በአንዳቸው የተጠራጠረ በእርግጥ በሁላቸውም የተጠራጠረ ነው፡፡ በኛ ላይ ጥርጣሬ ያደረበት ደግሞ በእሳት ውስጥ ይሆናል፡፡

ሰዎች ሆይ! ኃይልና አሸናፊው አላህ ተቆጥሮ በማይዘለቀው ችሮታውና ፀጋው ይህንን ክብር አጎናጸፈኝ፡፡ ከሱ በስቀር አምላክ የለም፡፡ ከዘመናት እስከ ዘመናት ለዝንተዓለም በማንኛውም ሁኔታ እጅግ አመሰግነዋለሁ፡፡

ሰዎች ሆይ! (ከሁሉም በላይ) ለዓሊ ብልጫ ስጡ፡፡ ከወንድም ሆነ ከሴት፣ አላህ ፀጋውን (በረከቱን/ ርዝቁን) መለገስ እስከቀጠለ ድረስና ፍጥረታት በህይወት እስካሉ ድረስ ከኔ በኃላ በላጩ ሰው እሱ ነውና፡፡ ይህንን ቃሌን የማይቀበልና

ያስተባበለ ሰው በእርግጥ እርጉም ነው፣እርጉም ነው፤ (በአላህ) ቁጣ ስር ነው፤ በአላህ ቁጣ ስር ነው (*መልዑኑን መልዑኑን፣ መገዱቡን መግዱቡን*)፡፡

እነሆ ጂብሪል ይህንን ጉዳይ አስመልክቶ ከአላህ ነገረኝ፡፡ እንዲህም አለኝ፡-***የዓሊ ጠላት ለመሆን የቢቃና መሪነቱን የተቃወመ (ያልተቀበለ) ሰው እርግማኔና ቁጣዬ በሱ ላይ ነው፡፡***

ስለዚህ እያንዳንዱ ሰው ነገ ለነፍሱ ምን እንዳዘጋጀ ያስብ፡፡ አላህን ከመቃወምና ከእምበተኝነት ተጠንቀቁ፡፡ እግራችሁ በደንብ መሬት ከያዘና ከተረጋጋ በኋላ እንዳይሸራተት ጥንቃቄ አድርጉ፡፡ አላህ የምትሰሩትን ሁሉ ጠንቅቆ ያውቃል፡፡

ሰዎች ሆይ! እሱ (ዓሊ) አላህ በቁርአኑ ውስጥ ያወሳው «የአላህ ጎን» ነው፡፡ አላህም እንዲህ ይላል፡-

***(የካደች) ነፍስ እኔ ከሚሳለቁት የነበርኩ ሰሆን፣ በአላህ ጎን ባጓደልኩት ዋ ጸጸቴ! ማለቷን (ለመፍራት) (39፡56)***

ሰዎች ሆይ! ቁርአንን አስተንትኑ፣አንቀጾቹም (አያዎቹን) በደንብ ተረዱ፡፡ ትኩረታችሁን ግልጽ በሆኑት አያዎቹ (*ሙህከማቲሂ*) ላይ አድርጉ፡፡ ግልጽ ያልሆነውንና አደናጋሪ የሆነባችሁ አያዎቹን (*ሙተሻቢሂሁ*) አትከተሉ፡፡ በአላህ እምላለሁ! ይህ በእጄ የያዝኩት፣ከፍ አድርጌ ከጎኔ ያቆምኩትና እጁን ከፍ አድርጌና ብድግ አድርጌ የማሳያችሁ ሰው፤እኔ ወሊይ (መሪ) የሆንኩት ማንኛውም ሰው ይህ ዓሊም ወሊዩ (መሪው) ነው ብዬ ያወጅኩት ይህ ሰው

ካልሆነ በስተቀር ማስጠንቀቂያዎቹንና ጥልቅ ሚስጢሮቹን (የቁርአን ማለት ነው) የሚያብራራላችሁና ተፍሲሩን (ትርጉም)ና ዝርዝር ጉዳዩን ግልጽ የሚያደርግላችሁ ማንም የለም፡፡ እነሆ ይህ ሰው ወንድሜና ወራሼ ዓሊ ቢን አቡ ጧሊብ ነው፡፡ መሪነቱን መቀበል (ሙዋላቱሁ) ከኃያሉና አሸናፊው አላህ የወረደ ግዴታ ነው፡፡

ሰዎች ሆይ! እነሆ ሁለት ከበባድ ነገሮችን በመካከላችሁ ትቻለሁ፡፡ እነዚህን ሁለት ነገሮች አጥብቃችሁ ከያዛችሁ ፍፁም ለጥመት አትዳረጉም፡፡ እነሆ ከቤተ-ዘሬ የሆኑት ንጹሀን ልጆቹ ከሁለቱ ከበባድ ነገሮች አነስተኛው ሲሆኑ ቁራአን ደግሞ ከፍተኛው ነው፡፡ እያንዳንዳቸው አንዱ ስለ አንዱ የሚናገር እና እርስ በርሳቸው የሚስማሙ ናቸው፡፡ በሐውድ (የጀነት ምንጭ) ላይ እስከንገናኝ ድረስ ሁለቱ በጭራሽ አይለያዩም፡፡

ልብ በሉ! እነሱ (አህለል ቤይት) በፍጥረታቱ ላይ የአላህ ተወካዬች ናቸው፣በምድሩ ላይም የጥበብ ባለቤቶች እና መሪዎች ናቸው፡፡
እነሆ በርግጥ ኃላፊነቴን ተወጥቻለሁ፣በርግጥ መልዕክቱን አድርሻለሁ፣ በርግጥ አስተላልፌያለሁ፣ በርግጥ አብራርቻለሁ፡፡ እነሆ ኃያሉና የላቀው አላህ ተናገረ፣ እኔም የሰማሁትን ተናገርኩ፡፡ እነሆ ***ከወንድሜ ሌላ ‹አሚረል ሙዕ ሚኒን›*** የለም፣ እነሆ ከኔ በኃላ ለሱ በስተቀር መሪነትና ኢማምነት ለአማኞች ሕገ ወጥ ነው፡፡

## ክፍል አራት

## ነቢዩ(ሰ.ዐ.ወ) የአሊን እጅ ከፍ አድርገው ያዙ

*የነቢዩ እጆች፣ በመድረኩ ላይ ከሳቸው ትንሽ ዝቅ ብለው በቀኛቸው በኩል የቆመውን የአሊ ቢን አቢ ጧሊብን ከንድ ከኹጥባው መጀመሪያ አንስቶ ይዘው ነበር፡፡ ከንዱ ስር ይዘው እግሩ ጉልበታቸው ጋር እስኪደርስ ድረስ ብድግ አድርገው ከያዙ በኃላ ንግግራቸውን ቀጠሉ፡፡*

ሰዎች ሆይ! ***ከነፍሶቻችሁ በላይ ቅድሚያ የምትሰጡት ለማን ነው ? (በራሳችሁ ላይ ካለችሁት ሙብት ይልቅ የበለጠ ሙብት በናንተ ላይ ያለው ማን ነው?)***

ሰዎችም ***አላህና መልዕክተኛው*** በማለት በአንድነት መለሱ፡፡

ነቢዩም(ሰ.ዐ.ወ)፡- እነሆ እኔ ወሊይ (መሪ) የሆንኩት ሰው ሁሉ ይህ ዓሊም ወሊዩ (መሪው) ነው፡፡ አላህ ሆይ እሱን ለተከተሉትና ለተወዳጁት ረዳትና ወዳጅ ሁንላቸው፣ ለሱ ጠላት የሆኑትን ጠላት ሁናቸው፣እሱን ለረዱና ለደገፉት ረዳትና ድጋፍ ሁናቸው፣ እሱን የካዱትንና የተውቱን አንተም ካዳቸው፣ ተዋቸው፡፡

ሰዎች ሆይ! ይህ ወንድሜና ወራሼ ዓሊ ነው፡፡ የዕውቀቴ ስልቻ እሱ ነው፡፡ በህዝቤና በኔ ያመኑ ሁሉ ላይ የተሾመ መሪ እንዲሁም የኃያሉንና አሸናፊውን የአላህ መጽሀፍ በመተንተነንና ወደ ቁርአን በመጥራት ተተኪዬ (ኸሊፋዬ) እሱ ነው፡፡ አላህ የሚወደውን ብቻ የሚሠራ፣የአላህን ጠላቶች የሚዋጋ፣ለአላህ

መታዘዝን የሚያዝና የሚያስፈጽም፣ ለአላህ የማይታዘዙትን የሚመክርና የሚመልስ እሱ ነው፡፡

እነሆ እሱ የአላህ መልዕክተኛ ኸሊፋ (ተተኪ)፣ አሚረልሙዕሚኒን (የአማኞች/ሙዕሚኖች አለቃና መሪ)፤ ኢማማል ሓዲ (ወደ ቅኑ መንገድ የሚመራ ኢማም)፤ ቃል ኪዳን አፍራሾችን፣አፈንጋጮችንና እምቢተኞችን የሚዋጋና የሚያጠፋ እሱ ነው፡፡

በአላህ ትዕዛዝና ስልጣን እናገራለሁ፡፡ በውስጤ ያለው ቃል አይቀየርም (የአላህ ቃል አይታጠፍም፣ አይቀየርም)፡፡

በጌታዬም ትዕዛዝ እላለሁ፡- ጌታዬ ሆይ ለለተከታዬቹ አንተ ጠባቂያቸው ሁናቸው፣ ለጠላቶቹ ጠላት ሁናቸው፣በተቃዋሚዎቹ ላይ እርግማንህን አውርድባቸው፣መብቱንና ሐቁን በሚክዱት ላይ ቁጣህን አውርድባቸው፡፡

አላህ ሆይ! እነሆ ***በዛሬው ዕለት ኃይማኖታችሁን ምሉዕና ፍጹም አደረኩላችሁ፣ፀጋዬንም በናንተ ላይ ሞላችሁላችሁ፣ ከኃይማኖትም ኢስላምን ወደድኩላችሁ፡፡ ከኢስላም ውጭ ሌላ ኃይማኖት የሚፈለግ ሰው ተቀባይነት የለውም፣በትንሳኤ ቀንም ከከሳሪዎች ይሆናል*** የሚለውን አያህ በዛሬው ዕለት መምረጥህንና መሾምህን በማስመልከት ለወሊይህ ለዓሊ ከወረድክ፡፡ አላህ ሆይ! (ይህን መልዕክት) ስለማድረሴ አንተን ምስክሬ አደርገሃለሁ! ጌታዬ ሆይ ምስክር ሁነኝ!

## ክፍል አምስት

## የህዝቡን ትኩረት ወደ ኢማምነት (ኢማማህ) ጉዳዮች መሳብ

ሰዎች ሆይ! ኃያሉና አሸናፊው አላህ ኃይማኖታችሁን ምሉዕና ፍጹም ያደረገው በዓሊ ኢማምነት (መሪነት) ሹመት ነው፡፡

ስለዚህ የሱንና ከሱ በኃላ ከቤተ-ዘሮቼና ከአብራኩ የሚወለዱትን የልጆቹን ተምሳሌት እስከ የውመል ቂያማ (የትንሳኤ ቀን) የማይከተሉ ሰዎች (የሰው ልጅ) ሥራቸው አላህ ፊት በሚቀርብበት ቀን ተግባራቸው ከንቱና ፍሬ አልባ ሆኖ በጀሐነም እሳት ውስጥ ለዘለዓለም የሚኖሩ ናቸው፡፡ ቅጣታቸው አይቀልላቸውም፣አይተላልፍላቸውም(አይዘገይላቸውም)፡፡

ሰዎች ሆይ! ይህ ከማንም በላይ ረዳቴና ደጋፊዬ፣ ከማንም በላይ እኔ ዘንድ ውድ የሆነ፣ከማንም በላይ የሚቀርብኝና ከማንም በላይ እኔ ዘንድ ተወዳጅ የሆነ ዓሊ ነው፡፡ ኃያሉና የላቀው አላህና እኔ በሱ ደስተኞች ነን፣ ወደንለታልም፡፡

በቁርአን ውስጥ ስለአላህ ውዴታ የሚያወሳ አያህ (አንቀጽ) ስለሱ ካልሆነ በቀር (እሱን አስመልክቶ እንጂ) አልወረደም፡፡

**እናንተ ያመናችሁ ሆይ** በማለት አላህ በቁርአኑ አማኞችን በክብር በሚጠራበት ጊዜ መጀመሪያ በሱ ሳይጀምር አንቀጾቹን ያ ወረደበት ጊዜ የለም፡፡ አወዳሽ (የሚያወድሱ) የቁርአን አንቀጾች ባሉበት ሁሉ ዓሊ አለበት፡፡

***ሐል አታ ዓለል ኢንሳኒ ሂኑን ምነደህሪ (ረዥም ዘመን በሰው ልጅ ላይ አላለፈም እንዴ?)*** በሚለው የቁርአን ምዕራፍ (ሱራህ) ውስጥ ጀነት የተመሰከረለትና የተወደሰ እሱ እንጂ ማንም አይደለም፡፡ ለሱ እንጂ ለሌላ ለማንም አልወረደም፡፡

ሰዎች ሆይ! የአላህ ኃይማኖትን የሚከላከልና የሚጠብቅ፣ በአላህ መልእክተኛ ቦታ ሆኖ የሚከራከርና የሚጋፈጥ እሱ ነው፡፡
እሱ ነው ጥርት ያለ ጻድቅና ወደ ቅኑ መንገድ የተመራ መሪ፡፡ ነቢያችሁ ምርጥ ነቢይ ነው፣ በናንተ ላይ የተወከለው ከሊፋዬም ምርጥ ኸሊፋ ነው፣ ልጆቹም ምርጥ ተወካዮችና ተተኪዎች ናቸው፡፡

ሰዎች ሆይ! ኢብሊስ አደምን በቅናት ከጀነት አስወጣ፡፡ ስለዚህ በሱ(ዓሊ) ላይ አትቅኑ (የቅናት መንፈስ አያድርባችሁ)፡፡ አለበለዚያ ሥራችሁ ከንቱ ይሆናል፣ እግራችሁም ይንሸራተታል፡፡ አደም የአላህ ወዳጅ ሆኖ ሳለ በአንዲት ስህተት ምክንያት ወደ ምድር ወረደ፡፡ ታዲያ እናንተ ደግሞ እናንተ ሆናችሁ ከእናንተም የአላህ ጠላቶች ባሉበት ሁኔታ ምን ትሆኑ ይሆን;

ልብ በሉ! ሸቂይ (ከአላህ ረህመት የራቀ ጠማማና ደረቅ) የሆነ ሰው ካልሆነ በስተቀር ዓሊን የሚጠላ ሰው የለም፡፡ ተቂይ (አላህን የሚፈራና ጻድቅ) የሆነ ሰው ካልሆነ በስተቀር ከሱ ጋር የሚወዳጅና የሚከተለው ሰው የለም፡፡ ትክክለኛና እውነተኛ አማኝ ካልሆነ በስተቀር በሱ የሚያምን የለም፡፡ በአላህ እምላለሁ ሱረህ አል-አስር (ወል አስር) የተሰኘው የቁርአን ምዕራፍ እሱን አስመልክቶ የወረደ ነው፡፡

***በጊዜያቱ እምላለሁ፤ ሰው ሁሉ በእርግጥ በከሳራ ውስጥ ነው፡፡ እነዚያ ያመኑትና መልካሞችን የሠሩት፣ በውነትም አደራ የተባባሉት፣ በመታገሥም አደራ የተባባሉት ብቻ ሲቀሩ፡፡ (103፡1-3)***

ሰዎች ሆይ! እነሆ መልዕክቴን ስለማድረሴ አላህ ምስክሬ ነው፡፡ የመልዕክተኛ ኃላፊነትና ግዴታ በግልጽ ማስተላልፍና ማድረስ ነው፡፡

ሰዎች ሆይ! አላህን መፈራት የሚገባውን ያህል ፍሩት ፡፡ እጅ ሳትሰጡ እንዳትሞቱ፡፡

## ክፍል ስድስት

### የሙናፍቆችን ዓላማና ሐሳብ መጠቆም

ህዝቦች ሆይ! በአላህና በመልዕክተኛው እመኑ፣ ከሱ ጋር (ከመልዕክተኛው ጋር) በወረደው ብርሃን (ኑር) እመኑ፡፡ ***ፊቶች ከመቀየራችንና ወደ ኃላዋ ከመመለሳችን በፊት እመኑ፣ ወይም ደግሞ የሰንበት (ሰብት) ህግ የጣሱትን ሰዎች እንደረገምናቸው እንርግማቸዋለን (4፡47)***

በአላህ አምላለሁ! በዚህ ቁርአን አያህ የታሰቡት ሰዎች ማንም ሳይሆን ከሰሃቦቼ የሆኑ በስማቸውና በዘር ሐረጋቸው የማውቃቸው ቡድኖች ናቸው፡፡ ነገር ግን ንቄ እንዳልፋቸው ታዥዣለሁ፡፡ እያንዳንዳችሁ ለዓሊ ጥላቻ በልቦቻችሁ ውስጥ ባለው መሠረት እንደፈለጋችሁ ማድረግ ትችላላችሁ፡፡

ሰዎች ሆይ! ከኃያሉና ጥበበኛው ጌታ የሆነው ብርሃን በኔ ውስጥ ተደርጓል፣ ከዚያ ደግሞ የአላህን ሐቅና የኛንም ሙብት ዳግም የሚያቋቁም የሆነው እስከ አል-ቃኢም አል-መህዲ ድረስ ከዓሊ በሆኑ ትውልዶች (ነሰል) ውስጥ ተደርጓል፡፡

ይኸውም ኃያሉ አላህ እኛን በመላው ዓለማት በሚገኙ ችላ ባዮች፣ ዋልጌዎች፣አፈንጋጮች፣ አታላዮች፣ ሐጢአተኞች (ወንጀሎች)፣ በዳዮችና ሙሰኞች ላይ ማስረጃና ወቢ አድርጎናልና፡፡

ሰዎች ሆይ! እኔ የአላህ መልዕክተኛ  መሆኔን አስጠንቅቃችኃለሁ፡፡ ከኔ በፊት የነበሩና ያለፉ መልዕክተኞች በእርግጥ ነበሩ፡፡ ታዲያ እኔ ከሞት ወይም ብገደል ወደ ኃላ ትመለሳላችሁን; ወደኃላው የሚመለስ ማንም አላህን ቅንጣት ሊጎዳ አይችልም፡፡ አላህ አመስጋኞችን (ትዕግስተኞችን) በቅርብ ይመነዳቸዋል፡፡

ልብበሉ! በአመስጋኝነት (ሹክር)ና በትዕግስት (ሰብር) ባህርያት የተገጸለውና የተወሳው ዓሊ ነው፡፡ ከዚያ በኃላ ደግሞ ከአብራኩ የተገኙ፣ ከኔ ቤተ ዘር የሆኑት ትውልዶች ናቸው፡፡

ሰዎች ሆይ! ኢስላምን በመቀበላችሁ ለአላህ ውለታ የፈጸማችሁ መስሎአችሁ አትንጠባረሩ፡፡ ቁጣው ይወርድባችሁና ከሱ የሆነ ቅጣት እንዳያጋጥማችሁ ተጠንቀቁ፡፡ በእርግጥ እሱ ምንግዜም ተመልካች ነው፡፡

ሰዎች ሆይ! እነሆ ከኔ በኃላ ህዝቡን ወደ እሳት የሚጣሩ መሪዎች ይመጣሉ፡፡ በፍርዱ ቀን የሚረዳቸው የለም፣ አይረዱምም፡፡ ሰዎች ሆይ! አላህና እኔ ከነሱ የጠራን ነን፡፡

ሰዎች ሆይ! እነዚህ ሰዎች፣ ረዳቶቻቸው፣ ተከታዮቻቸውና ቡድኖቻቸው በጀሀነብ እሳት ውስጥ የመጨረሻው አረንቋ ውስጥ ይሆናሉ፡፡ የአፈንጋጮችንና ተንጠባሪሪዎች መመለሻ ምንኛ የከፋ ነው! እነዚህም በእርግጥ ***የመዝገቡ ሰዎች*** (**አስሀበሰሂፋህ**) መሆናቸውን እወቁ፡፡

እያንዳንዳቸው (የሥራ) መዝገቡን (ሰሂፋውን) ይመርምር፡፡

እዚህ ላይ ኢማም ሙሀመድ አል-በቂር ሲናገሩ ይህንን የመዝገብ (ሰሂፋህ) ጉዳይ በተመለከተ ከጥቂት ሰዎች በስተቀር (እራሳቸው መዝገቡ ሰዎች የነበሩ ሰዎች በስተቀር) አብዛኛው ሰው ምን እንደሆነ አልተረዱም ነበር::

ሰዎች ሆይ! ከኔ በኃላ ያለውን የኢማምነት (መሪነት) ስልጣን እስከ ፍርዱ ቀን (የውመል ቂያማህ) ድረስ የቤተዘሮቼ ውርስ አድርጌ ትቻለሁ፡፡ በቅርቡ ባለውም ሆነ ሩቅ ባለው ሰው፣ በቀጥታ የመስከረም ሆነ ያልመሰከረ (በቦታው ተገኝቶ የታደመም ሆነ ያልታደመ)፣ የተወለደም ሆነ ገና የሚወለድ ሰው ላይ ማስረጃ ይሆን ዘንድ እንዳታስተላልፍ የታዘዝኩትን መልዕክት አድርሻለሁ፡፡ የሰማ ላልሰማ ያሰማ፣ የነበረ ሰው ላልነበረው ያስተላልፍ፣ ወላጆች ለልጆቻቸው ይተርኩ፡፡ ትውልዱ እየተቀባበለ እስከ ቂያም ቀን ድረስ ያስተላልፍ፡፡

ነገር ግን የተወሰኑ ሰዎች ይህንን (በመለኮታዊ ትዕዛዝ የተቋቋመ መሪነት) ሞስነው ወደ ንጉሳዊ የአምባገነን አገዛዝ እንደሚለውጡ (ተነግሮኛል)፡፡ እነሆ የአላህ እርግማን በሙሰኞችና ቀማኞች ላይ ይውረድ!

ከዚያም፣ ***እናንተ ሁለቱ ከባባዶች ሆይ! (አዩሀስሰቀላን)! ጉዳያችሁን በቅርቡ እናስተናብራለን፡፡ (55፡31)***

እንዲሁም ***እናንተ ሁለቱ (ጠላቶች) ሆይ! በናንተ ላይ ደግሞ የእሳት ወላፈንና የቀለጠ መዳብ ይላክባችሁና ፍጹም ድል እንዳታገኙ ትሆናላችሁ፡፡ (55፡35)***

ሰዎች ሆይ! አላህ በጎውን ከመጥፎው (መልካሙን ከእርኩሱ) ሳይለይ አሁን ባላችሁበት ሁኔታ ውስጥ በፍጹም አይተዋችሁም፡፡ በማታውቁት ነገር (በሩቁ ዕውቀት/ በገይብ) ላይ ተጠያቂ አያደርጋችሁምም፡፡

ሰዎች ሆይ! እነሆ ከእውነት ያፈነገጠና ሐቅን አሻፈረኝ የሚል አንድም ከአላህ ቅጣት የሚያመልጥ ማህበረሰብ አይኖርም፡፡ ሐቅን በመካዳቸውና በማስተባበላቸው ምክንያት አላህ ከዚያም ቀን በፊት ያጠፋቸዋል፡፡

አላህ (በቁርአኑ ውስጥ) እንደተናገረው ብልሹ ህብረተሰቦችን በዚህ መልኩ ያጠፋቸዋል፡፡ ይህ ኢማማችሁና ወሊያችሁ (መሪያችሁ) ነው፡፡ እነዚህ ህብረተሰቦች በሙሉ በኢማም አል-መህዲ ይገዛሉ፡፡ አላህ የገባውን ቃል የሚፈጽም ጌታ ነው፡፡

ሰዎች ሆይ! ከናንተ በፊት ከነበሩት ትውልዶችም አብዛኞቹ የጠመሙና ያፈነገጡ ነበሩ፡፡ አላህ እነዚህን ቀደምት ትውልዶች በእርግጥ አጠፋቸው፡፡ እሱ ከዚያ በኃላ የመጣውንም ትውልድ የሚያጠፋ ነው፡፡ ኃያሉ አላህ እንዲህ ይላል፡-

***የቀድሞ ትውልዶችን አላወደምናቸውን? የኋለኛውንም ትውልድ እናስከትላለን፡፡ ከእውነት ያፈነገጡትን (ሙጅሪሞችን) እንዲህ ነው የምናደርጋቸው፡፡ በዚን ዕለት እውነትን መቀበል አሻፈረን ላሉ ሰዎች ወየውላቸው! (77፡16-19)***

ሰዎች ሆይ! አላህ በአንዳንድ ነገሮች አዘዘኝ፣ከአንዳንድ ነገሮች ደግሞ ከለከለኝ (ትዕዛዛትንና ክልከላዎችን ሰጠኝ)፡፡ እኔ ደግሞ በአላህ ትዕዛዝ መሰረት ዓሊን በአንዳንድ ነገሮች አዘዝኩት፣ ከአንዳንድ ነገሮች ደግሞ ከለከልኩት (ትዕዛዛቱንና ክልከላዎቹን ሰጠሁት)፡፡

ስለዚህ የማዘዝና የመከልከል ዕውቀት ከሱ (ዓሊ) ጋር ነው፡፡ ትድኑ ዘንድ ትዕዛዛቱን ስሙ፣(ወደ ቅኑ መንገድ) ትመሩ ዘንድ ታዘዙት፣ መልካም ስብዕና እንድትጎናጸፉና እንድታቃኑ እሱ ከከለከላችሁ ነገር ተከልከሉ፣ ከሐሳቡ ጋር ተስማሙ፡፡ የተለያዩ መንገዶች ከሱ ጎዳና እንዲለዩዋቸው አትፍቀዱ፡፡

## ክፍል ሰባት

## የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) አህለልቤይት (ቤተሰቦች) ወዳጆችና ጠላቶች

ሰዎች ሆይ! ትከተሉት ዘንድ በአላህ የታዘዛችሁት የአላህ ቀጥተኛው መንገድ ነኝ እኔ፡፡ (ከኔ በኃላ) ቀጣዩ ሰው ደግሞ ዓሊ ነው፡፡ ከዚያ በኃላ ደግሞ ከዓሊ አብራክ የሆኑ ቤተዘሮቼ (ውልዲ) ናቸው፡፡ በሐቅ የሚመሩ ኢማሞችና በሐቅ የሚተገብሩ እንዲሁም ሰዎችን ወደ ሐቅ የሚመልሱ መሪዎች ናቸው፡፡

ከዚያ በኃላ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሱረቱል ፋቲሃን (አልሐምዱ ሊላኒ ረቢል ዓላሚንን) ከመጀመሪያው ጀምረው እስከ መጨረሻው ከቀሩ በኃላ እንዲህ አሉ፡-

ይህ (የቁርአን ምዕራፍ) የወረደው እኔንና እነሱን (ኢማሞቹን) በአጠቃላይም ሆነ በተናጠል በማስመልከት ነው፡፡ እነዚህ ፍርሃትና ሐዘን የማይነካቸው ሹመት የተጎናጸፉ ናቸው፡፡

ልበ በሉ! ድል የሚጎናጸፉትና አሸናፊዎች የአላህ ፓርቲዎች/ወገኖች (ህዝበላህ) ናቸው፡፡ እነሆ ጠላቶቻቸው ደግሞ አፈንጋጮች፣ በዳዮች፣ እምቢተኞችና እርስ በርሳቸው በአጉል ቃላት ደባና አሻጥርን ለማስፋፋት ነገር የሚቀባበሉ የሰይጣን ወንድሞች ናቸው፡፡

እነሆ የቅርብ ወዳጆቻቸው ደግሞ አላህ በቁርአኑ ውስጥ ያወሳቸው እውነተኞቹ አማኞች (ሙዕሚኑን) ናቸው፡፡ ኃያሉና ጥበበኛው አላህ እንዲህ ይላል፡-

*በአላህና በመጨረሻው ቀን የሚያመኑትን ሕዝቦች አላህንና መልዕክተኛውን የሚከራከሩትን ሰዎች አባቶቻቸው ወይም ልጆቻቸው፤ ወይም ወንድሞቻቸው ወይም ዘመዶቻቸው ቢሆኑም እንኳ የሚወዳጁ ሆነው አታገኛቸውም፤ እነዚያ በልቦቻቸው ውስጥ እምነትን ጽፏል፤ ከርሱም በሆነ መንፈስ ደግፏቸዋል፤ ከስሮቻቸውም ወንዞች የሚፈሱባቸውን ገነቶች በውስጣቸው ዘውታሪዎች ሲሆኑ ያገባቸዋል፤ አላህ ከነርሱ ወዷል፡፡ ከርሱም ወደዋል፤ እነዚያ የአላህ ሕዝቦች ናቸው፤ እነሆ የአላህ ሕዝቦች እነሱ ምኞታቸውን የሚያገኙ ናቸው፡፡ (58፡22)*

እነሆ የቅርብ ወዳጆቻቸው ኃያሉና የላቀው አላህ እንዲህ በማለት ያወደሳቸው ናቸው፡-

***እነዚያ ያመኑና እምነታቸውን በበደል ያልቀላቀሉ፣ እነዚያ ለነርሱ ጸጥታ አላቸው፤ እነሱም የተመሩ ናቸው፤ (6፡82)***

በእርግጥም የቅርብ ወዳጆቻቸው ***እነዛ ያመኑትና (በእምነታቸው ውስጥ) ምንም ዓይነት ጥርጣሬ ያላደረባቸው ናቸው*፡ *(49፡15)***

እነሆ የቅርብ ወዳጆቻቸው ***እነዛ በሰላም ጀነት የሚገቡ ናቸው፡፡ መላዕኮችም እንኳን ደስ ያላችሁ! ምንኛ አማራችሁ! ግቡ፣ለዘለዓለምም በውስጧ ኑሩ እያሉ በሰላምታ ይቀበሉዋቸዋል (39፡73)***

እነሆ ወዳጆቻቸው ***እነዛ ጀነት የሚገቡና በዉስጧ ያለ ሀሳብ ሲሳያቸውን የሚቀበሉ*** በማለት ኃያሉ አላህ ያወሳቸው ናቸው፡፡

እነሆ ጠላቶቻቸው እነዛ ሰኢር (ጀሀነም) የሚደርሱ ናቸው፡፡ በእርግጥ ጠላቶቻቸው እነዛ የጀሀነምን ጉርምርምነትና የወላፋኑን ድምጽ፣ ስቅታውንና ንፍርቁን፣ ሲቃውንና ትንፋሹን የሚሰሙ ናቸው፡፡

ልበ በሉ! ጠላቶቻቸውማ አላህ በቁርአኑ እንዲህ በማለት የገለጻቸው ናቸው፡-
***አንደኛዋ ህዝብ ውስጧ በገባች ጊዜ ሁሉ ሌላኛዋ እህቷን ትራገማለች (7፡38)፡፡***

እነሆ ጠላቶቻቸውማ አላህ እንዲህ በማለት የገለጻቸው ናቸው፡-
***ከቁጭትዋ የተነሳ፣ ልትቆራረጥ ትቀርባለች፤ በውስጧ ጭፍሮች በተጣሉ ቁጥር ዘበኞችዋ አስፈራሪ (ነቢይ) አልመጣችሁምን? በማለት ይጠይቋቸዋል፡፡ አይደለም በእርግጥ አስፈራሪ መጥቶናል፤ አስተባበልንም፤ አላህም ምንንም አላወረደ፤ እናንተ (አውርዷል ስትሉ) በትልቅ ስሕተት ውስጥ እንጅ አይደላችሁም አልን፤ ይላሉ፡፡ የምንሰማ ወይም የምናስብ በነበርንም ኖሮ በነዳጅ እሳት ጓዶች ውስጥ ባልሆን ነበር ይላሉ፡፡ (67፡8-11)***

እነሆ ወዳጆቻቸው ግን ***እነዛ ጌታቸውን በሩቁ ( በሚስጢር ) የሚፈሩ ሲሆኑ ምህረትና ታላቅ ሽልማት ያለላቸው ናቸው (67፡12)፡፡***

ሰዎች ሆይ! በሚለበልብ እሳት (ሰኢር)ና በታላቅ ሽልማት (አጅሩን ከቢር) መካከል ምን ያህል የሰፋ ልዩነት አለ!

ሰዎች ሆይ! ጠላቶቻችን አላህ የሚተቻቸውና የሚረግማቸው ሲሆኑ ወዳጆቻችን ደግሞ አላህ የሚያውድሳቸውና የሚወዳቸው ናቸው፡፡

ሰዎች ሆይ! ልብ በሉ - እኔ አስጠንቃቂ (ሙንዚር) ነኝ፣ ዓሊ ደግሞ መሪ (ሃዲ) ነው፡፡

ሰዎች ሆይ! እኔ ነቢይ ነኝ፣ ዓሊ ደግሞ ወራሼ ወይም ጉዳይ አስፈጻሚዬና ወኪሌ (ወሲዩ) ነው፡፡

ሰዎች ሆይ! እኔ የአላህ መልዕክተኛ ነኝ፣ ዓሊና ተከታዮቹ ልጆቹ ደግሞ ኢማሞችና ወራሾቼ ናቸው፡፡ እነሱ ከዓሊይ አብራክ የተገኙ ሲሆኑ በእርግጥ እኔ አባታቸው ነኝ፡፡

## ክፍል ስምንት

## ኢማም አል-መህዲ

አስተውሉ! ከኛ የሆነው የኢማሞች መደምደሚያ አል-ቃኢም አል-መሀዲ ይሆናል፡፡ እነሆ እሱ በኃይማኖቱ ላይ የበላይነትን ይጎናጸፋል፡፡ አጥፊዎችን የሚቀጣና ምሽጎችንና የኀያላን ቤተ- መንግስታትን የሚቆጣጠርና የሚያወድም ነው፡፡

እነሆ የእያንዳንዱን የሽርክ ሰዎች (አህል አል-ሺርክ) ቡድኖችን የሚያጠፋ እሱ ነው፡፡

የኃያሉ አላህ አውሊያዎችን (በምድር ላይ የአላህ ወኪሎች/መሪዎችን) ጠላቶች የሚበቀልና ደማቸውን የሚመልስ እሱ መሆኑን ልብ በሉ፡፡

የአላህ ኃይማኖት (ዲን) ረዳትና የድል ባለቤት ይሆናል፡፡
(የሰዎችን ድርሻ) ከጥልቅ ባህር (እውቀቱና ከመለኮታዊ ምንጮች) የሚያወጣ እነሆ እሱ ነው ፡፡

እያንዳንዱን ሰው፣ ባለ ማዕረጉን እንደማዕረጉና ደረጃው፣ መኃይማንና አላዋቂዎችን እንደ ማኃይምነታቸው በደረጃቸው የሚሰይምና ሁሉንም በአቅሙ የሚፈርጅ ይሆናል፡፡

ልብ በሉ! እሱ የአላህ ሊቅ ነው፣ የመረጠውም አላህ ነው (መራጩም አላህ ነው)፡፡
እነሆ እሱ የሁሉም ዕውቀት ወራሽ ይሆናል፣ ሁሉንም ጥበብ (ፈህም) የሚያካብብና የሚጠቀልል ይሆናል፡፡
እነሆ እሱ የአሸናፊውና ጥበበኛው አላህ ወኪል ሆኖ ስለ እምነት (ኢማን) የሚመከር፣ መረጃ የሚለግስና የሚያስጠነቅቅ ይሆናል፡፡
እነሆ እሱ ስልጣንና ኃይል የተጎናጸፈ፣ ከስህተት የፀዳ፣ እንከን የለሽ አዕምሮ የተቸረው መሪ ይሆናል፡፡

ልብ በሉ! ሁሉም ያለፉ (ነቢያት) ስለሱ ብስራት ሰጥተዋል፡፡
እነሆ እሱ የአላህ ቀሪ ማስረጃ ነው፣ ከሱ በኋላ (አዲስ) ማስረጃ አይኖርም፡፡

እነሆ ሐቅ ከሱ ጋር በስተቀር አይኖርም፣ ከሱ ካልሆነ በስተቀር (ወደ ቅን የሚመራ) ብርሃንም አይኖርም፡፡

እነሆ እሱ በምድር ላይ ስልጣን የተጎናጸፈ የአላህ ኸሊፋ ይሆናል፡፡ በምድር ላይ የአላህ ኸሊፋ፣ በፍጥረታት ላይ የአላህ ፈራጅና በገሃዱም ሆነ በድብቁ የአላህ ወኪል ይሆናል፡፡

## ክፍል ዘጠኝ

## ሰዎች ቃል-ኪዳን እንዲገቡና ምስክርነታቸውን እንዲሰጡ (በይዓ እንዲያደርጉ) ማነሳሳት

ሰዎች ሆይ! እነሆ በእርግጥ በግልጽ ነገርኳችሁ፣ ከአላህ የመጣውንም ትዕዛዝ በሚገባ እንድትረዱ አድርጌያለሁ፡፡ ከኔ በኃላ ደግሞ ስለ እያንዳንዱ ነገር እንድትረዱ የሚያደርጋችሁና ስለሁሉም ነገር የሚገልጽላችሁ ይኸው ይህ ዓሊ ነው፡፡

ንግግሬን እያገባደድኩ መሆኔን እንድታውቁ እፈልጋለሁ፡፡ ይህንን ንግግሬን ሲጨርስም ቃለ መሐላ እንድትፈጽሙና ለተሰጠው ሹመትና ስልጣን ምስክርነት ትሰጡ ዘንድ በመጀመሪያ ከኔ ጋር እጅ እንድትጨባበጡ፣ ከዚያም ደግሞ ከሱ (ዓሊ) ጋር እንድትጨባበጡ እጠራችኃለሁ፡፡

እነሆ እኔ በእርግጥ ለአላህ ቃሌን ሰጥቻለሁ (በይዓ አድርጌያለሁ)፣ ዓሊ ደግሞ ለኔ ቃሉን ሰጥቷል (በይዓ አድርጓል)፡፡ እኔ ደግሞ ከአላህ በመጣው ትዕዛዝ መሠረት እነሆ ለሱ (ዓሊ) ቃል-ኪዳን እንድትገቡ (በይዓ እንድታደርጉ) እጠይቃችኃለሁ፡፡ ሀያሉና ጥበበኛው አላህ እንዲህ ይላልና፡- ***እነዚያ ቃል ኪዳን የሚጋቡት፣ አላህን ብቻ ነው፤ የአላህ እጅ፣ (ኃይሉ) ከእጆቻቸው በላይ ነው፤ ያፈረሰም ሰው የሚያፈርሰው በነፍሱ ላይ ብቻ ነው፤ በእርሱ ላይ አላህን ቃል ኪዳን የተጋባበትን የሞላም ሰው ታላቅ ምንዳን በእርግጥ ይሰጠዋል፡፡ (48፡10)***

## ክፍል አስር

## የኃይማኖት ህግጋት መጠናቀቅና የኢማሞቹ ሚና

***ሰዎች ሆይ! ታላቁና ታናሹ ጉዞ (ሐጅና ዑምራ)፣ የሰፋና መርዋ (ተራራዎች) ከአላህ ምልክቶች ናቸው፡፡ በወቅቱም ሆነ በሌሎች ጊዜያት የአላህን ቤት ለመጎብኘት የሚሄድ ሰው (ሐጅና ዑምራ የሚያደርግ ሰው) (በሁለቱ የሰፋና መርዋ ተራራሮች) መካከል በተደጋጋሚ ቢዘዋወር (ጠዋፍ ቢያደርግ) ምንም ጥፋት አላጠፋም (ምንም ችግር የለውም)፡፡*** (2፡158)

ሰዎች ሆይ! የአላህን ቤት ጎብኙ (ሐጅ አድርጉ)፡፡ ለሐጅ በመውጣት መብቃቃትንና ብስራትን ያገኘ ቤተሰብ እንጂ ሌላ የለም፡፡ ወደ ኃላ በመቅረት ደግሞ ያደኅየ እንጂ የለም፡፡

ሰዎች ሆይ! በመቆሚያው ቦታ (የአረፋት በረሃ) ማንም አማኝ (ሙዕሚን) አይቆምም እስከዚያ ጊዜ ድረስ የሰራው ወንጀል (ሀጢአት) ሁሉ እዛ ቦታ በመቆሙ የሚማርለት ሰው ካልሆነ በስተቀር፡፡ በዚያን ወቅት ከሀጢአቱ በሙሉ ነፃ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ልክ የሐጅ ተግባሩ ሲያልቅ ደግሞ የሥራ መዝገቡ እንደገና ይጀምራል ማለት ነው፡፡

ሰዎች ሆይ! የአላህን ቤት ጎብኚዎች (ሐጅ አድራጊዎች/ሐጃጆች) እርዳታን ያገኛሉ፡፡ ያወጡት ወጪም ተመላሽ ይደረግላቸዋል፡፡ አላህ የመልካም ሠሪዎችን ምንዳ አያባክንምና፡፡

ሰዎች ሆይ! የተሟላና ፍጹም የሆነ እምነት/ዲን (በዓሊ ዊሊያ አማካይነት) ይዛችሁና ኃይማኖትን በሚገባ የተረዳችሁ ሁናችሁ የአላህን ቤት ጎብኙ (ሐጅ አድርጉ)፡፡ ንስሃ ሳትገቡ (ሳትቶብቱ) ና ከሁሉም ሐጢአት ሳትጸዱ ከዚህ የተቀደሰ ቦታ ተመልሳችሁ አትሂዱ፡፡

ሰዎች ሆይ! ሀያሉና የበላይ የሆነው አላህ እንዳዘዛችሁ ሰላትን ቀጥ አድርጋችሁ አቁሙ፣ ዘካን ክፈሉ (ስጡ)፡፡ በጊዜ ቆይታ ምክንያት እውቀት ቢያጥራችሁ ወይም ብትረሱ እንኳ መሪያችሁ ዓሊ ሁሉን ነገር ያብራራላችኃል፡፡ እሱ (ዓሊ) ከኔ በኃላ በፍጥረታት ላይ ጠባቂ አድርጎ አላህ የመረጠው ሰው ነው፡፡ እሱ ከኔ ነው፣ እኔም ከሱ ነኝ (እነሁ ሚንኒ ወአነ ሚንሁ)፡፡

እሱና ከኔ *ዘርሪያ* (ቤተዘር) የሆኑ ተተኪዎቹ ለምትጠይቁት ነገር ሁሉ መልስ ይሰጡአችኋል፣ የማታውቁትንም ግልጽ ያደርጉላችኋል፡፡

በእርግጥ እዚህ ቦታ ላይ የተከለከሉ ነገሮችን (ሐራም)ና የተፈቀዱ ነገሮችን (ሐላል) ለመዘርዘርና ድንበራቸውን ለመወሰን እንዲሁም በሐላል ላዛችሁና ከሐራም ልመከራችሁ እጅግ ብዙ በመሆናቸው በዚህ አንድ ቦታ ሁሉንም ለማንሳት አያመችም፡፡

ስለዚህ አሚረል ሙዕሚኒን ዓሊንና ከኔና ከሱ የሆኑትን ተተኪዎቹን ኢማሞች አስመልክቶ ከሀያሉና የላቀው አላህ የመጣውን ትዕዛዝ ስለመስማታችሁና መቀበላችሁ ማረጋገጫ ከናንተ ቃል-ኪዳን እንዲቀበል (በይዓ እንድወስድ) ታዝዣለሁ፡፡

ሰዎች ሆይ! (በዚህ የምርጫ/ በይዓ ሥነ-ሥርዓት አማካይነት) ወደ ሁሉም ሐላል ነገሮች አመላከታችኃለሁ፣ ከሁሉም ሐራሞችም ከልክያችኃለሁ፡፡ በዚህ ላይም ወደ ኃላ ተመልሼ ፍጹም ቃሌን አላጥፍም፣ ምንም የምይቀይረውና የምተካው ነገርም በጭራሽ አይኖርም፡፡

ስለዚህ ልብ በሉ! ይህንን አስታውሱ፣ አጥብቃችሁም ያዙ፡፡ በዚህ ላይ ምስክር ተሰጣጡ፡፡ በሌላ ነገር ፍጹም አትቀይሩ፣ አትተኩም፡፡
እነሆ ደጋግሜ እናገራለሁ፡- ሰላትን ቀጥ አድርጋችሁ አቁሙ፣ ዘካንም ክፈሉ፡፡ በመልካም ነገር እዘዙ፣ ከመጥፎ ነገር ከልክሉ፡፡

እነሆ በመልካም ነገር የማዘዝ ዋነኛው ተግባር ይህን ቃሌን ሰምታችሁና ተረድታችሁ ላልሰማው መስማት፣ ሰምተው እንዲቀበሉ ማዘዝና የሚቃወሙና

የሚቃረኑትን መከልከልና ማስጠንቀቅ ነው፡፡ጉዳዩ የኃያሉና አሸናፊው አላህ ና የኔ ትዕዛዝ ነውና ፡፡

እንከን የለሽ (መዕሱም የሆነ) ለሆነ ኢማም እጅ መስጠትና ዕውቅና መስጠት በሌለበት ሁኔታ ከመጥፎ  ነገር መከልከልም ሆነ በበጎ ነገር የማዘዝ ተግባር ትርጉም የሌለው መሆኑን እወቁ፡፡

ሰዎች ሆይ! ከሱ (ዓሊ) በኃላ ያሉ ኢማሞች (መሪዎች) ከሱ የሚወለዱና የልጅ ልጆቹ እንደሆኑ ቁርአን በግልጽ ያሳውቃችኃል፡፡ እነዚህ ኢማሞች ከኔና ከሱ ስለመሆናቸው በተደጋጋሚ አሳውቂያችኃለሁ፡፡ ኃያሉና የበላይ የሆነው አላህ በመጽሀፉ (ቁርአን) ውስጥ እንዲህ ይላል፡-

***በሱ ትውልድ (ቤተዘር) ውሰጥ የምትፀና ቃል አደረጋትም***(43፡28)

ሰዎች ሆይ! አላህን ፍሩ፣ አላህን ፍሩ! አላህ እንዳለው ሁሉ ያችን ሰዓት (ሳዓህ) ተጠንቀቁ!

***በእርግጥ የሰዓቷ መናወጥ እጅግ ከባድ ነገር ይሆናል (22፡1)***

ሞትን፣ትንሳዔን፣ መመርመርን (ሂሳብ)፣(የፍትህ) ሚዛንን፣ የዓለማት ጌታ ፊት መቆምን፣ ሽልማትንና ቅጣትን አስታውሱ/ አስቡ!

የቂያም ቀን በጎ ሥራ ይዞ የሚመጣ ሽልማት ያገኝበታል፡፡ (ምህረት የሌለው) እኩይ ተግባር ይዞ የሚመጣ ሰው ከጀነቶች ድርሻ የለውም፡፡

## *ክፍል አስራ አንድ*

## *ቃል- ኪዳኑን በቃል ማሰማትና በይዓ (ቃለ-መሐላውን) መቀበል*

“ሰዎች ሆይ! ከሁላችሁም ጋር በአንዴ ለመጨባበጥ እጅግ ብዙ ስለሆናችሁ አይመችም፡፡ ለዓሊ የሰጠሁትን ሹመትና ከሱ ቀጥሎ ለሚመጡት ኢማሞች የተሰጠውን ቦታ በአጠቃላይ መስማታችሁንና መቀበላችሁን፣ የኔ አህለል ቤይት (ቤተዘሮች) ከዓሊ አብራክ የሚገኙ መሆናቸውን እንደነገርኳችሁና እንደ ተቀበላችሁ የሚያረጋግጥ ቃላችሁን በአፋችሁ በማሰማት ቃል ኪዳን መግባታችሁን (በይዓ ማድረጋችሁን) ቃላችሁን እንዲቀበል ከሁሉ በላይ የላቀው ጌታ አዞኛል፡፡ ስለዚህ ሁላችሁም እንዲህ በሉ፡-

ኢማማችንና መሪያችን አሚረል ሙዕሚኒን ዓሊንና ከርስዎና ከርሱ አብራክ የሆኑትን ኢማሞች አስመልክቶ ከርስዎና ከኛ ጌታ ከሆነው አላህ ያደረሰከንን መልዕክት ሰምተን፣ ወደን ተቀብለን፣ እጅ ሰጥተን ታዝናል፡፡ በልቦቻተን፣ በነፍሶቻችን፣ በምላሶቻችነና በእጆቻችን ቃለ መሀላ በማድረግ ምስክርነታችን እንሰጣለን፡፡ በዚህ ቃላችን ላይ እንኖራለን፣ እንሞታለን፣ እንቀሰቀሳለን፡፡ መሐላችንን አንቀይርም፣ ሌላ ተተኪም አንፈልግም፣ አንጠራጠርም፣ አንክድም፣ አናወላውልም፣ ቃላችንን አናጥፍም፣ ቃል ኪዳናችንንም አናፈርስም፡፡

አሚሩል ሙዕሚኒኒ ዓሊን እንዲሁም ከርስዎ ቤተሰብ የሆኑትንና ከዓሊ አብራክ የተገኙትን ሐሰንና ሁሴንን እንዲሁም ከነርሱ ቀጥሎ የሚመጡትን የተነገሩንን

ኢማሞች አስመልክቶ ያደረሱን መልዕክት ከአላህ የሆነ መልዕክት መሆኑን እንመሰክራለን፡፡ ለነርሱ የገባነው ቃልና የሰጠነው ምስክርነት ከልቦቻችን፣ ከነፍሶቻችን፣ ከምላሶቻችን፣ ከአዕምሮአችን፣ ከእጆቻችንና ከአካላችን በሙሉ የተወሰደ ነው፡፡ በእጅ ማድረግ ባንችልም በምላስ አረጋግጠናል፡፡

በሌላ በማንም አንለውጥም፣ ቃላችንን አናጥፍም፡፡ ልጆቻችንንና ዘመዶቻችንን ጨምሮ ቅርብ ላሉት ሰዎችም ሆነ ሩቅ ላሉት ሁሉ መልዕክቱን እናደርሳለን፡፡ በዚህ ላይ ጌታችን አላህ መስካሪ ይሆን ዘንድ እንለምናለን፡፡ የአላህና የመልዕክተኛው ምስክርነት ምንኛ በቂና ያማረ ነው!"

አንተም በኛ ላይ መስካሪ ነህ፣እንዲሁም ትዕዛዙን የተቀበሉ በሙሉ በግልጽ የሚታዩም ሆነ ድብቅ የሆኑ ኃይሎች፣ የአላህ መላዕካዎችና ሌሎች ኃይሎችና አገልጋዮች ሁሉ በኛ ላይ መስካሪዎች ናቸው፡፡ አላህ ከሁሉም መስካሪዎች በላይ ነው፡፡

ሰዎች ሆይ! ታዲያ ምን ትላላችሁ? አላህ እያንዳንዷን ድምጽ የሚሰማና የእያንዳንዷን ነፍስ ሚስጢር ውስጠ-አዋቂ ጌታ ነው፡፡

***ቅኑን መንገድ የተከተለ ለራሱ ጥቅም ነው፣ ከቅኑ መንገድ ያፈነገጠም እራሱን ነው የሚጎዳው፡፡*** (39፡41)

እነዛ ቃል- ኪዳን የገቡትና ቃለ-መሐላ የፈጸሙት (በይዓ ያደረጉት) ሰዎች ቃል የገቡት ለኃያሉ አላህ ነው፣ የአላህ እጅ ከእጃቸው በላይ ነው፡፡

ሰዎች ሆይ! አላህን ፍሩ፣ ለአሚራል ሙዕሚኒን ዓሊ(ዐ.ሰ.) ለሐሰን፣ ለሁሴይንና ከነሱ ከሚወለዱ ተከታይ አኢማዎች(መሪዎች) - በቋሚነት የምትፀና መልኳሚ ቃል- በይዓ አድርጉ ( ቃል-ኪዳን ግቡ)፡፡

አታላዮችንና አስመሳዮችን አላህ ያጠፋቸዋል፡፡ በታማኝነታቸው ፀንተው እውነተኝነታቸውን የሚያስመስከሩትን አላህ ይምራቸዋል፡፡

ስለዚህ ***ቃል-ኪዳኑን ያፈረሰ /የካደ በእርግጥ የራሱን ነፍስ ነው የካደው፡፡ ከአላህ ጋር የገባውን ቃል-ኪዳን ጠብቆ ያሟላ ደግሞ አላህ በቅርቡ ታላቅ ሽልማት ያጎናጽፈዋል***፡፡ (48፡10)

ሰዎች ሆይ! የነገረኳችሁን በሉ! ዓሊን ***አሚረል ሙዕመኒን*** በሚል የማዕረግ ስም ሰላምታ አቅርቡለት፡፡

እንዲህም በሉ፡- ***ሰማን፣ ታዘዝንም፡፡ ጌታችን ሆይ! ምህረትህን እንሻለን፡፡ መመለሻችን ወደ አንተ ነው (ወደ ቅጣትህ ወይም ሽልማትህ ነው መመለሻችን)***፡፡ (2፡285)

እንዲህም በሉ፡- ***ለዚህ ላበቃንና ወደዚህ የመራን ጌታ ምስጋና የርሱ ነው፣ እሱ ባይመራን ኖሮ ለዚህ አንበቃም ነበር፡፡ ቅኑን መንገድም አንመራም ነበር***፡፡ (7፡43)

ሰዎች ሆይ! አላህ በቁርአን የገለጻቸው የዓሊ ቢን አቢ ጧሊብ ፋዲላዎች (ዝናና በላጭነት) እጅግ በርካታ በመሆናቸው በዚህ በአንድ ቦታ ተቆጥሮ የሚዘለቅ አይደለም፡፡ ማንም ሰው ስለፋዲላው ቢተርክላችሁና ቢያሳውቃችሁ እመኑት፡፡

ሰዎች ሆይ! አላህን፣ መልዕክተኛውን፣ ዓሊንና የጠቀስኳቸው ኢማሞችን የሚታዘዝ በእርግጥ ታላቅ ስኬትንና ብልጽግናን የተጎናጸፈ ዕድለኛ ነው፡፡

ሰዎች ሆይ! ከናንተ ለዓሊ በእውነት ቃል-ኪዳን ለመግባት (በይዓ ለማድረግ) ቀዳሚ የሆኑትና መሪነቱን በመቀበልና ***አሚረል ሙዕሚኒን*** (የአማኞች መሪ) በሚለው የማዕረግ ስም ሠላምታ ለማቅረብ የተሽቀዳደሙና ቀደምትነቱን የወሰዱ የደስታና ሐሴት ጓሮዎች (ጀነቱንነዒም) ባለዕድሎችና ስኬታማዎች ናቸው፡፡

ሰዎች ሆይ! አላህ ከናንተ የሚወድላችሁን ቃል ተናገሩ/በሉ፡፡ እናንተም ሆናችሁ በምድር ላይ ያለው በሙሉ በአላህ ብትክዱ (ብትከፍሩ) አላህን ቅንጣት ታህል እንደማትጎዱ እወቁ፡፡

አላህ ሆይ!(ባደረስኩት መልዕክትና ባዘዝኳቸው) ያመኑትን ምህረትህን ለገሳቸው፡፡

በከሃዲዎችና አፈንጋጮች ላይ ቁጣህ ይውረድባቸው!

***ምሥጋና ሁሉ ለዓለማት ጌታ ለአላህ ነው፡፡***

## ኢድ አል-ገዲር (የገዲር በዓል)

የገዲር በዓል የነቢዩ ቤተዘሮች (አህለል በይት) በዓል ነው፡፡ በኢስላም ውስጥ እጅግ የገዘፈ ታሪካዊ ቀንን ታሳቢ በማድረግ የሚከበር ዓመታዊ በዓል ነው፡፡ ገዲር በሰማይ ነዋሪዎች ዘንድ ***የታላቁ ቃል-ኪዳን ቀን*** ተብሎ የሚታወቅ የጌታ በዓል ነው፡፡ ገዲር የደስታ ቀንና አላህ ኃይማኖቱን ምሉዕና ፍጹም ያደረገበትና ፀጋውን በሰው ልጆች ላይ የሞላበት የሐሴት ዕለት ነው፡፡

## የገዲር በዓል በታሪክ ውስጥ

ገዲር ለመጀመሪያ ጊዜ በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የአስተዳደር ዘመን ስለተከበረ ታሪኩ በኢስላም ውስጥ ሥር የሰደደ ቦታ አለው፡፡ መጀመሪያ የተከበረው ከመሰናበቻው ሐጅ በኋላ በዕለተ-ገዲር ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ኸሊፋቸውን (ተተኪያቸውን) የመረጡ ጊዜና በኃይማኖቱ መሠረቶች ላይ አጠቃላይ ገለጻ ባደረጉበት በዛ ታሪካዊ ቀን ነበር፡፡
ሁሉም ሙስሊሞች የተባረኩበት ድንቅ ቀን ነበር፡፡ የኢስላማዊ ህግጋት ማዕከልና የመመሪያዎቹ ህልውና የሆነ ታላቅ ሰው የተመረጠበት እጅግ ወሳኝ ዕለት ነበር፡፡

ስለዚህ እውነተኛ ሙስሊሞች በአላዋቂዎችና መኃይማን በሚናፈሰው የድንቁርናና የአፈንጋጭነት በሽታ በመታለል ከዚህ ቅዱስ ቀን መዘናጋት የለባቸውም፡፡

*ወደ አላህ የሚወስደው ቀጥተኛው መንገድ በግልጽ የተገለፀበት በመሆኑ ይህ ዕለት በተፈጥሮ እጅግ ታላቅ ቀን መሆን አለበት፡፡ ቁርአን እንደሚገልጸው፣ ይህ ዕለት ኃይማኖቱ ምሉዕና ፍጹም የሆነበትና መለኮታዊ ፀጋ የተሟላበት ቀን ነው፡፡*

በዚህ ምክንያት አሚረል ሙዕሚኒን ዓሊ ይህን የተከበረ የመሪነትና የአላህ ህግጋት አስፈጻሚነት ቦታ በመጎናጸፉ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለዓሊ የእንኳን ደስ አለህ መልካም ምኞት እንዲቀርብለት ለህዝቡ ትዕዛዝ አስተላለፉ፡፡

ሙስሊም ያልሆነ ጣሪቅ ቢን ሺሓብ የተባለ ሰው እንኳ ይህን አቋም ተረድቶ ነበር፡፡ ለኸሊፋ ኡመር ቢን አል-ኸጣብና አብረውት ለነበሩ ሰዎች ጣሪቅ እንዲህ ብሏቸው ነበር፡-

***"በዛሬው ቀን ኃይማኖታችሁን ምሉዕና ፍጹም አደረግኩላችሁ፣ ፀጋዬንም በናንተ ላይ ሞላሁ፣ ኢስላምንም እንደ ኃይምኖት ወደድኩላችሁ"*** የሚለው የቁርአን አያህ በኛ ላይ የወረደ ቢሆን ኖሮ ይህንን ዕለት በዓል አድርገን እንይዘው ነበር፡፡"

## የገዲር በዓል እጅግ አስፈላጊነት

በዕለቱ የተከሰቱ ነገሮችና ሁኔታዎች ለዚህ ቀን የላቀና የመጠቀ ቦታ ሰጥተውታል፡፡ ለመልዕክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) የመለኮታዊ ተልዕኮ መደምደሚያና ለቅን መንገድ መሪ ኢማሞችና ለተከታዮቻቸው ደስታና ሐሴትን ያጎናጸፈ ዕለት ነበር፡፡ ዕለቱን የምናከብርበት ዋናው ምክንያት ይህ ነው፡፡

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡-

"የገዲር ቀን ከህዝቤ የበዓላት ቀናት ውስጥ በላጩና ታላቁ ነው፡፡ ይህ ቀን ወንድሜ ዓሊ ቢን አቢ ጧሊብ ከኔ በኋላ የህዝቡ መሪ ሆኖ እንዲመረጥ በኃያሉ አላህ የታዘዝኩበት ቀን ነው፡፡ በተጨማሪም ኃያሉ አላህ ኃይማኖቱን ምሉዕና ፍጹም ያደረገበት፣ ፀጋውን በህዝቦቹ ላይ የሞላበትና ኢስላምን እንደ ኃይማኖት የመረጠበት ቀን ነው፡፡"

የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) ፋና በመከተል አሚረል ሙዕሚኒን ዓሊ (ዐ.ሰ) ዕለቱን በበዓልነት ያከብር ነበር፡፡ እንከን የለሾቹ ኢማሞችም ዕለቱን ያከብሩ ነበር፣ ሙስሊሞችም እንዲያከብሩና በዕለቱ መልካም ነገሮችን መስራት ያለውን ጥቅምና ትሩፋት በመግለጽ ይመክሩ ነበር፡፡

በታሪክ ውስጥ ይህ ድንቅ ባህል ተጠብቆ ቆይቷል፡፡ የኢስላም ህዝብ ጠብቆ አቆይቶታል፡፡ ቀጣዩ ትውልድም የዛን ዕለት ክስተት እንደ ክብረበዓል እያከበሩ ኖረዋል፡፡ የዛን ዕለት ዋዜማ ሌሊት በአምልኮ፣ በፍቅርና በአድናቆት ያሳልፉ ነበር፡፡

በተጨማሪም በዛን ቀን በተለየ ሁኔታ መልካም ተግባራትን በመሥራትና ጥሩ ሥነ-ምግባራትን በማንፀባረቅ፣ የተቸገሩትን በመርዳትና በማስደሰት በደስታ ያሳልፉ ነበር፡፡

## በበዓሉ ዕለት የሚደረጉ ነገሮች

ከኢማሞቹ የተነገሩ በርካታ ሐዲሶችን መሰረት በማድረግ፣ በርካታ ማህበራዊ ዕንቅስቃሴዎች በዕለቱ መደረግ አለባቸው፡፡ የእንኳን ደስ አለንን መልዕክት በመለዋወጥ፣ ዕለቱን የሚያስታውሱና የሚወክሉ ግጥሞችን፣ መዝሙሮችንና ንግግሮችን በማቅረብ ውስጣዊም ሆነ ዉጫዊ ደስታችንን መግለጽ፡፡ በተጨማሪም የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) ቤተዘሮች (አህለልቤይት) ዝናና ፈዲላ (በላጭነት) በማውሳት፣ ሰለዋት በማውረድና ጠላቶቻቸውን ደግሞ በመኮነንና በመራገም ዕለቱን ማሳለፍ አለብን፡፡ መጠያየቅ (መዘያየር)፣ ስጦታ መለዋወጥ፣ በስራችን ለሚተዳደሩ ሰዎች የፈለጉትን መስጠትና የተቸገሩትን መርዳት በዕለቱ በይበልጥ እንዲሰሩ ከሚመከሩ ተግባራት ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

በተጨማሪም በግል የሚከናወኑ በርካታ ተግባራት አሉ፡፡ እነዚህም ማጋጌጥ፣ አዳዲስ ልብሶችን መልበስ፣ ዋዜማውን በአምልኮ ማሳለፍ፣ በዕለቱ መጾም፣ ዱዓዕ ማድረግ፣ በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እና በአህለል ቤይታቸው ላይ ሰለዋት ማውረድና በጠላቶቻቸው ላይ እርግማን ማውረድና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

አሚረል ሙዕሚኒን ዓሊ (ዐ.ሰ) በሚጎበኝበት (በሚዘየርበት) ወቅት የሚቀሩ (የሚባሉ) ነገሮችን መቅራት በዕለቱ ከሚመከሩ ነገሮች አስፈላጊው ነው፡፡ ይህ የተገባውን ቃል-ኪዳን (በይዓ) በመደጋገም ማደስ፣ በመሪነቱ በማመን መጽናትና ኢማሞችን በመታዘዝ ለሱ ታማኝ ሆኖ መጽናትን ያመለክታል፡፡

## የመጨረሻ ቃል

በአሥራ ስምንተኛው ዙልሂጃህ ላይ የሚውለውን ይህንን የገዲር ዕለት አስመልክቶ ዳኢዎች (ሚሺነሪዎች) የዚህን ዕለት ዝርዝር መረጃ እንዲሰጡና ኹጥባውን እንዲቀሩ አሳስባለሁ። ሁሉም ሙስሊሞች ኹጥባውን መላልሰው የማጥናትና መልዕክቱን ለማስተላለፍ ኮፒውን የመያዝ ግዴታ አለባቸው።

ይህንን ተግባር በመፈጸም ኃላፊነትን መወጣት ከአላህ የመጣውን መለኮታዊ ሹመት አስመልክቶ የተገባውን ቃል-ኪዳን (በይዓ) ለህዝቡ ተደጋግሞ ይደርስ ዘንድ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ያስተላለፉትን ትዕዛዝ ተቀብሎ መተግበር ነው። ለመለኮታዊ መሪነቱ ታማኝ በመሆን ሰዎችም ታማኝ እንዲሆኑ ማስተላለፍ ነው። እነሱም ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ)፣ አሚረል ሙዕሚኒን ዓሊ፣ ፋጡማ አል-ዘህራና እንከን የለሾቹ (መዕሱም የሆኑት) ኢማሞች ናቸው። በሁላቸውም ላይ የአላህ ሰላምና በረከት ይውረድ።

## የነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የመጨረሻው
## ህዝባዊ ንግግር (ኹጥባ) ሙሉ የዐረቢኛ ጽሁፍ

بِسْمِ اللهِ الرَّحْمنِ الرَّحيمِ

### 1. الحمد والثناء

الْحَمْدُ للهِ الَّذي عَلا في تَوَحُّدِهِ وَدَنا في تَفَرُّدِهِ وَجَلَّ في سُلْطانِهِ وَعَظُمَ في أَرْكانِهِ، وَأَحاطَ بِكُلِّ شَيْء عِلْماً وَهُوَ في مَكانِهِ، وَقَهَرَ جَميعَ الْخَلْقِ بِقُدْرَتِهِ وَبُرْهانِهِ، حَميداً لَمْ يَزَلْ، مَحْمُوداً لا يَزالُ وَمَجيداً لا يَزُولُ، وَمُبْدِئاً وَمُعيداً وَكُلُّ أَمْر إِلَيْهِ يَعُودُ.

بارِئُ الْمَسْمُوكاتِ وَداحِى الْمَدْحُوّاتِ وَجَبّارُ الاْرَضينَ وَالرُّوحِ، مُتَفَضِّلٌ وَالسَّماواتِ، قُدُّوسٌ سُبُّوحٌ، رَبُّ الْمَلائِكَةِ عَلى جَميعِ مَنْ بَرَأَهُ، مُتَطَوِّلٌ عَلى جَميعِ مَنْ أَنْشَأَهُ. يَلْحَظُ كُلَّ عَيْن وَالْعُيُونُ لا تَراهُ.

كَريمٌ حَليمٌ ذُو أَناة، قَدْ وَسِعَ كُلَّ شَيْء رَحْمَتُهُ وَمَنَّ عَلَيْهِمْ بِنِعْمَتِهِ. لا يَعْجَلُ بِانْتِقامِهِ، وَلا يُبادِرُ إلَيْهِمْ بِمَا اسْتَحَقُّوا مِنْ عَذابِهِ.

